# እኩዮች እና እንከፎች

ራስ አርዲ
ጥቅምት 2009

*መግቢያ*

በሀገራችን ከምርጫ 1997 በኋላ የታየው የሕዝብ የለውጥ ፍላጎትና ተነሳሽነት፣ ከዚያም ከአስር ወራት በፊት በኦሮሞ ወጣቶች ተቀጣጥሎ በአማራ ሕዝብ የቀጠለው ሕዝባዊ እንቢተኝነት ይሄው ዛሬም በአመራር ክፍተት የተነሳ እየተንገዳገደ ይገኛል፡፡ ችግሩን ተረድተው አመራር መስጠት የሚገባቸው ግለሰቦችና ድርጅቶች በተለመደው የእኩይነትና የእንከፍነት ባህሪያቸው የተነሳ ለመተባበር፣ ለመነጋገርና ሁሉንም የሚያግባባ መፍትሄ ፈልጎ ወደ ፊት በሰላም ለመራመድ አልደፈሩም፡፡ የደፈሩትንም የሚያጣጥል፣ ተስፋ የሚያስቆርጥና ውስጥ ለውስጥ የሚቦረቡር እንጂ አይዟችሁ፣ ይቻላል ተባብረን ለሁላችንም ወደሚመች ሥርዐት እንሸጋገራለን ባይ ክፍል ገኖ መውጣት አልቻለም፡፡ በዚህ መሃል እየተዋደቀና እያለቀ ያለው ሕብረተሰብ የለውጥ ፍላጎቱ እየከሰመ እንደከዚህ በፊቱ ሁሉ አንገቱን ለመድፋት እተገደደ ነው፡፡ ለዚህ ሁሉ ተጠያቂዎቹ ከላይ የተጠቀሱት በሁሉም ወገን ቁም ነገር የሌላቸው እኩይና እንከፍ ግትሮች ናቸው፡፡ ሕዝብ ቀድሟቸው ሄዶ አብሮነትን፣ ፍቅርን፣ ይቅር ባይነትና ትእግስትን እየተዋደቀና እየሞተ በተደጋጋሚ ቢያሳያቸውም አሁንም ሊነቁለት አልቻሉም፡፡ ያሳዝናል!!!

ሰሞኑን በኢሬቻ ክብረበዓል ላይ የደረሰውን እልቂት ተከትሎ እየታየ ያለውን የሕዝብ አመፅና ያገሪቱን አለመረጋጋት ወደ ሰላማዊ ውጤት ለማሸጋገርና ይህቺን ያልታደለች አገር ከከፋ አደጋ ለማውጣት ከየትኛውም ወገን ግልፅ የሆነ ሕዝብ ሊያውቀው የሚገባ ጥረት ሲደረግ አልታየም፣ አልተገለፀም፡ ፡ የሚከፋፍል እንጂ የሚያቀራርብ ሁኔታ አይታይም፡፡ ቡድኖችና ተምረናልና አገር መምራት ይገባናል የሚሉ ግለሰቦች በየቡድናቸው ተነጣጥለው እየተፋጠጡ ነው፡፡ ከዚህም ጋር የምዕራቡ አለም ዝምታ ከተጋረጠው አደጋ አንፃር ሲታይ፣ ሊከተል የሚችለውን ትርምስና መተላለቅ የሚፈልገው ይመስላል፡፡ ግትር መንግስት፣ ደረቅ የፖለቲካ መሪዎች፣ ከጥቅሙ ሌላ ምንም የማይታየው የውጭ እጅ ባንድ ወገን፣ በሌላው ወገን ደግሞ ተቀፍድዶ የተያዘና ትግስቱ የተሟጠጠ ሕዝብ፡፡ ሊከተል የሚችለው አደጋ አሳሳቢ ነው:: ከዚህ በታች የሚገኘው ፅሁፍ ይህን ሁኔታ ወደ ከፍተኛ አደጋ እንዲሸጋገር የሚተጉትን እኩይና እንከፍ ወገኖች ለመውቀስ የተዘጋጀ መልእክት ነው፡፡

*‹‹… ብዙ ሕዝቦች፤ ያለፈውን፤ አይነት አገዛዝ፤ ከነመሪዎቹ አጥፍተው፤ ሌላ ገዥ ሲፈጥሩ፤ ያለሥራ ያለህብረትና ያለነጻነት ሊከናወን የማይቻለውን መልካም እድል የደረሱበት ይመስላቸዋል፡፡ ግን አድረው ውለው ሲያመዛዝኑት፤ አንድ ሕዝብ በመተባበር የጭቆናን ቀንበር እያሰወገደ በኅብረትና በብርታት በመስራት በፍቅርና በሰላም በመራመድ እንጂ፤ ሥልጣንን የሚሹ ገዢዎች በተለዋወጡ ቁጥር፤ የሚሰጡትን የትንፋሽ ተስፋና ባለፉት መሪዎች ላይ የሚያወርዱትን ነቀፋ፤ ሲመገቡ በመኖር መልካም እድል እንደማይገኝ ይረዱታል፤ ›› - አቤ ጉበኛ - አልወለድም አራተኛ እትም ሚያዝያ 2006 ዓ/ም*

በዚህ ፅሁፍ ውስጥ የምጠቀምባቸውን ኃይለ ቃሎች አይተው፣ አንባቢዎች እንደየግል አመለካከታቸው ሊረኩ፣ ሊገረሙ፣ ሊረበሹ፣ ሊበሳጩ ወይንም ሊደናገጡ ይችላሉ፡፡ በቁም ነገር ዙሪያ ማንዣበቡን ትቶ ቀጥተኛ መልእክት የሚያሰተላልፍ የብሶት፣ የምሬት፣ የቁጭትና፣ የእልህ ኡኡታ ነው፡፡ በታመቀ የመገፋት ስሜት፣ ውስጣዊ ንዴት፣ መሪር ሃዘንና ብስጭት ተገፋፍቶ ባገራችንና በሕዝባችን ላይ የተጫነውን የክህደት ቀንበር አስከፊነት የሚያጋልጥ ወቀሳ ሲሆን፤ በሚሸነቁጡ ቃላትም ሃገር በመሸጥ፣ ወገን በመበደልና በማስበደል ላይ ለሚገኙት የዘመናችን ልክ-አልባ እርጉሞች እያደረሱ ላሉት ጥፋት የሚገባቸውን የአፀፋ መልእክት የሚያስተላልፍ የወቀሳ ናዳ ነው፡፡

ከተለመደው ለዘብተኝነት፣ አንገትን በቅልስልስነት መድፋት፣ ማስመሰል፣ ያሰቡትን በግልጽና በቀጥተኝነት ከማስፈር ይልቅ ነገሮችን በማድበስበስ በሃገራችን ያዋቂነት ምልክት ነው እየተባለ ተቀባይነትን ያገኘ አጉል ልምድ ለየት በማለቱ የሚናደዱ፣ የሚጨነቁና የሚርበተበቱ ብዙ ሊኖሩ እንደሚችሉ እገምታለሁ፡፡ አላማዬም በደንብ እንዲደነግጡ፣ እንዲሰማቸው፣ ሕዝብና አገርን በእኩይነትም ሆነ በእንከፍነት ጎራ ተሰልፈው የበደሉና እየበደሉ የሚገኙት እርኩሶች የጥፋታቸውን አስከፊነት እንዲረዱት፣ ዝም ብለው የሚያዩትም ነፈዞች ለችግሩ ትኩረት ሰጥተው ከተኙበት እንዲነቁ ለመገፋፋት ነው፡፡ የሚነቃ ከተገኘ!!!! ዝም ብሎ መጠቃት፣ አገር ሲጠፋ እያዩ ችላ ማለት፣ ምንም ማድረግ አልችልም ብሎ እጅ አጣጥፎ መቀመጥ፣ የሃገራችን ጠላቶችና የሃገራችንን ሀብት በመመዝበር ላይ የሚገኙት፣ እንዲሁም ለከፋ

ምዝበራ አሰፍስፈው የሚጠባበቁት ቡድኖች እኛ እንድንሆንላቸው የሚፈልጉትን የደነዝነት፣ የራስ ወዳድነት፣ የጠባብነት፣ የስግብግብነት፣ የቸልተኝነት፣ የእኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል ባይነትና ባጠቃላይ የዘመናዊ ባርነትን ባሕሪ ማበረታታት መሆኑን ልንገነዘብ ይገባናል፡፡

ሃገራችን ኢትዮጵያ ባንድ ወገን ሕወሃት/ወያኔ/ኢሕአዴግ ብለው ራሳቸውን በሚጠሩ፤ ሃገራቸውንም፣ ወገኖቻቸውንም፣ ስብእናቸውንም በሸጡ፣ ቂም-በቀል በሚባል የአእምሮ በሽታ ታውረው ከራስ ወዳድነት፣ ከአጥፊነት፣ ከመሰሪነት፣ ከጨለምተኝነት፣ ከከፋፋይነት፣ ካውዳሚነት፣ ከከይሲነት፣ ከምቀኝነትና ከጎጠኝነት ሌላ ምንም ጥሩ ነገር በማይታያቸው እኩይ ዘመናዊ የመንደር ዱሩዬ ባንዳ አገር አጥፊዎች የፌጥኝ ተይዛ ወደ ዘላቂ ትርምስ፣ ውድቀትና ዘመናዊ ቅኝ ግዛትነት እየተገፋች ትገኛለች፡፡ በሌላ ወገን ደግሞ ምኞታቸው አስካልተነካና ጥቅማቸው እስካልጎደለ ድረስ ምንም አይነት የወገንም ሆነ የሃገር ጥቃት የማይሰማቸው በቂም በቀል የደነዘዙ፣ የነፈዙና ለጥቅም የሰከሩ እንከፎች ለመሰሪዎች ስውር ተልዕኮ ድጋፍ ሰጪ ሆነው አገሪቱን አያስቦረቦሯት ይገኛሉ፡፡

ያገሪቱ ያመራር መድረክ ባጉል ትምክህት በተወጠሩ ምሁር ነን ባይ ዲያቢሎሶች፣ እንዲሁም በዝቅተኝነት ስሜት በታጀሉና እነሱ ያሰቡት የበቀል እርምጃ እስካልተሳካ ድረስ ሃገሪቱን ለመገነጣጠልና ለማውደም ቆርጠው በተነሱ ጠባብነት የሚያጠቃቸው ተማርን ባይ አጋንንቶች ተሞልቶ ሕዝብ የመሪ ያለህ በሚልበት ወቅት ሕዝቧ የሚመኘውን አመራር መስጠት የሚገባቸው ክፍሎች በሚያሳዝን ሁኔታ ተከፋፍለውባት በተስፋ መቁረጥ ጎዳና እንድታዘግም እያስገደዷት ነው፡፡  በዚህም የተነሳ ዛሬ አገሪቱ በትምክሕት፣ በምቀኝነትና በዝቅተኝነት ስሜት ተገፋፍተው ጥፋቷን የሚመኙ እርጉም የእንግዴ ልጆች፣ የጠላቶቿና የዘመናዊ ቅኝ ገዢዎች መፈንጫ፣ የርካሽ ሸቀጥ ማራገፊያ፣ የክፉ ባሕል መስፋፊያ፣ የተገዢነት፣ የዝቅተኝነት ስሜትና ቅጥ ያጣ ሙስና ማዕከል በመሆን ነፃነቷ፣ ክብሯና ሕልውናዋ ለማንኛውም ተጫራች በመቸብቸብ ላይ ነው፡፡ ብሔራዊ ክብሯ ተገፎ ማንም ርካሽ ህሊና ቢስ ባለጊዜ እንደፈለገ የሚያረክሳት፤ ተገን ሊሆናት የሚችል፣ ጥቅሟንና ክብሯን የሚያስጠብቅላት ወገን በእንጭጩ እየተቀጨ፣ እየተከፋፈለና ተስፋ እንዲቆርጥ እየተደረገ፣ ራሱን የናቀና ተገዢነትን ያለምንም ማመንታት የሚቀበል የሰው አረም እንዲፈላባት የተገደደች የርካሽ አለም-አቀፍ ዘመናዊ ምዝበራ መልእክተኞች መፈንጫና መጫወቻ ሆናለች፡
፡

እዚህ ላይ -- እኩይ ና እንከፍ --የሚሉትን ቃላት ባገራችን ከኛ ሌላ አገር ለመምራት አቅሙም፣ ችሎታውም፣ እውቀቱም ያለው ‹‹የተቀባ›› ቡድን ማንም ሊኖር አይችልም በሚል አጉል እብሪት፣ ትምክህትና ጉራ ተወጥረው አገር ለሚያተራምሱት ሥልጣን ላይ የሚገኙ መሰሪዎችና፣ አገራቸውና ሕዝባቸው ላይ የሚፈፀመውን አስከፊ በደል እያዩና አየሰሙ እንደጋሪ ለሚጎተቱት ምሁራን ነን ባይ ወኔ ቢሶች መገለጫነት ተገቢ ናቸው በሚል የእርግጠኝነት ስሜት ተጠቅሜባቸዋለሁ፡፡  ቃላቶቹን እንድጠቀምባቸው የገፋፋኝ ምክንያት ሁለቱም ቡድኖች ባለፉት አመታት በተደጋጋሚ ያሳዩት የዘረኘኝነት፣ የመሰሪነት፣ የሆዳምነት፣ የስግብግብነት፣ የእብሪተኛነት፣ የንዝህላልነት፣ ያስመሳይነት፣ የወላዋይነት፣ የምቀኝነት፣ የከሃዲነት፣ ያድር ባይነት፣ የውሸታምነት፣ የችላ ባይነትና የግትርነት ጠባያቸው ነው፡፡ ሃገራቸውን ለቂም በቀል፣ ለግል ጥቅም፣ ለምቀኝነት፣ ለጎሰኝነት አሳልፈው ለሸጡት መሪዎች ነን ባዮችና፣ ይህንን ቅጥ ያጣ ያገርና የወገን ውርደትና ሽያጭ ተቀብለው ያለምንም ቁንቀትና የህሊና ወቀሳ ሃገራቸው ስትጠፋ፣ ስትዘረፍ፣ ስትዋረድ፣ ስትከፋፈልና ስትደፈር እያዩ እርስ በርስ ለሚሻኮቱት ደነዝ አወቅን ባዮች ልዩ መገለጫዎች እንዲሆኑ መርጫቸዋለሁ፡፡

እኩይ የሚለው ቃል ክፉ፣ መሰሪ፣ አጥፊ፣ እርጉም በማለት ይተረጎማል፡
፡ እንከፍ የሚለው ቃል ደግሞ ቂል፣ ጅል፣ ሞኝ፣ ከርፋፋ ማለት
ሲሆን ነፈዝነትን፣ ታጥቦ ጭቃነትንና፣ ንዝህላልነትን ያመለክታል::
በእኩይነትና በእንከፍነት ሕመም የተለከፉ ቡድኖችና ግለሰቦች ሃገራችን ላይ ከፍተኛ ጥፋት በማስከተል ላይ ናቸው፡፡እነዚህ ሁለት ቡድኖች ያገራችንን የፖለቲካ መድረክ በጎሳ ልጅነትና በወዳጅነት ተቆጣጥረው እርስ በርስ በመደጋገፍ ጥፋታችንንና ያገራችንን የውድመት ቀን እያፋጠኑት ይገኛሉ፡
፡  ምንም እንኳን የተሰለፉት በተለያየ ጎራ ቢመስልም አንዳቸው ለሌላው መጠቀሚያ በመሆን የሃገር ጉዳይ ወደ ጎን ተትቶ አስተዳደርና ያመራርሃላፊነት መንፈሰ-ደካማ እኩዮችና እንከፎች ለጊዜያዊ ጥቅማቸው፣ ለቂም በቀል ጥማታቸውና ለአጥፊ አጀንዳቸው ማራመጃ፤ በሚያስገምት ማይምነት፣ ብልግናና እብሪት የሚራኮቱበት የወሮ በሎችና ተምረው እውቀትን ያልቀሰሙ ማይማን መፈንጫ መድረክ አድርገውታል፡፡

ባንድ ወገን በእውቀትና በችሎታ ሳይሆን የዓለም የፖለቲካ ሁኔታ በፈጠረላቸው አጋጣሚ እብሪትን ከተራ ጉልበት ጋር አጣምረው ስልጣን የጨበጡትን አጋሰሶች፤ በሌላ ወገን ደግሞ ስልጣን ለመያዝና ቂም ለመወጣት ሲክለፈለፉ እርስ በርስ በመሻኮት ያገራቸውን ሕዝብ የስቃይ ዘመን በማራዘም ላይ የሚገኙትን የቀን ጅቦች ያጠቃልላል፡፡ እንዴት አድርጌ ልለያችሁ? እንዴው በእውነት ልዩነት አላችሁ? አገር መግደልና ፍቃድ ሰጥቶ ማስገደል ምን ልዩነት አለው? አገሩን ፈቅዶ የሚያስገድለው ከገዳዩ ምን ያህል ይለያል? ገዳይም አስገዳይም የወንጀሉ ተጠያቂ መሆናቸው የማያጠያይቅ ጉዳይ ነው፡፡

ሁላችሁም ወራዶች ናችሁ፣ ስግብግቦች ናችሁ፣ እርጉሞች ናችሁ፣ ሃላፊነት የማይሰማችሁ አርቃችሁ ማሰብ ያቃታችሁ፣ በምቀኝነት፣ በእብሪትና በቂም በቀል መንፈስ የምትነዱ ግትሮችና ደነዞች ናችሁ:: ሥልጣን በጉልበት የሙጥኝ ያላችሁት እርጉሞች የተለየ አላማ ይዛችሁ ዙፋን ላይ ቁጢጥ ስላላችሁ፣ በአላማችሁ ፀንታችሁ ቆዳችሁን እንደ መርዛም እስስት እየቀያየራችሁ የምትመኙትን በትምክህት የተወጠረ የበላይነት በኢትዮጵያ የጥፋት አመድ ላይ ያሳካችሁ ሰለመሰላችሁ ራሳችሁን ወደ መቀመቅ እየላካችሁ ትገኛላችሁ፡ ፡ ሌሎቻችሁ ደግሞ፣የተወሰናችሁት ትምክህት ስለሚያጠቃችሁ በጥቃቅን ያመለካከት ልዩነቶች ሰትሻኮቱ፣ የተቀራችሁት ደግሞ የዝቅተኝነት ችግር ስላለባችሁ በጠባብ አመለካከታችሁ በጎሳና በጎጥ ልጅነት ተከፋፍላችሁ መብቴን በጎሳዬ ዙሪያ ተደራጅቼ አስከብራለሁ እያላችሁ ታላዝናላችሁ፡፡ አላማችሁና ግባችሁ ምን እንደሆነ የምትከፋፍሉት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊገባው አልቻለም፡፡ አንድነቱን በተግባር በተደጋጋሚ ቢያሳያችሁም እናንተ ግን ከግትር አላማችሁ ፍንክች ሳትሉ በመሻገት ላይ ናችሁ፡፡ ለሃያ አምስት አመታት ያካሄዳችሁትን የተናጠል ጉዞ ውጤት አልባነት መረዳት ያልቻላችሁ፣ ተማርን የምትሉ፣ እውነተኛውን እውቀት ግን መቅሰም ያልሆነላችሁ ባለዲግሪ ማይሞች፡፡ ለሥልጣን ከመሯሯጥና ሆዳችሁን ለመሙላት ከማስመሰል ወይም ቂም በቀል ለመወጣት በእንስሳ መንፈስ እየተመራችሁ ከመሯሯጥ ሌላ አርቆ የማሰብ ቅንጣት ያህል ችሎታ እንደሌላችሁ እየተመሰከረላችሁ ነው፡፡ የባንዳ ተልእኮ ይዘው የመጡት እኩዮች በጎን ገብተው እርስ በርስ በጎሳ፣ በሃይማኖት፣ በክልልና በቋንቋ ለያይተው እያባሏችሁ የማይገባቸውን ስልጣን ተደላድለውበት የፈለጉትን እያደረጉ መሆኑ የሚገባችሁ መቼ ይሆን?

ፍቅር፣ መተሳሰብ፣ ቅን መንፈስ፣ ሕብረትና መከባበር ስላጣችሁም ሀገሪቱ የተሻለ አመራር እንዲኖራት የሚያስችል ሁኔታ መፍጠር አልቻላችሁም፡፡ ሁላችሁንም--እኩዮችንና የጎሳና የቡድን እንከፎች--የሚያመሳስላችሁ አንድ ጠባይ ቢኖር ያው የተለመደው ከረሃብ፣ ከድርቅ፣ ከስደትና ከልመና ቀጥሎ ያገሪቱ ሕዝቦች መለያ የሆነው የእርስ በርስ ምቀኝነታችሁ ነው፡፡ የጎሳና የቡድን እንከፎች ከምታደርጉት ሁኔታ ሲታይ አላማችሁ ለኛም አይሳካልን ለናንተም አይሳካላችሁ ሁላችንም እንደ ትቢያ በሆዳችን እየተንፏቀቅን ስንጠላለፍ ኖረን አብረን ተቀብረን እንቀራለን ይመስላል፡፡ እኛ እርስ በርስ ተሳስበን ከምንጠቃቀም፣ ከኛ በጥቃቅን ሁኔታ ይለያሉ የምንላቸው እህት ወንድሞቻችን ከሚያልፍላቸው፣ ባንዳዎችና ባእዳን እየመዘበሩን አገር ብትጠፋ ግድ አይለንም፣ የምንፈልገው ቂም በቀል ካልተሳካ አብሮ ከመኖር መበታተን ይሻላል ባዮች ናችሁ፡፡ እናንተ ስትናናቁ፣ ስትመቀኛኙ፣ ሰትወነጃጀሉና እርስ በርስ ለመጠፋፋት ስትሸርቡ፣ ባእዳንና አገር በቀል ከሃዲዎች አገራችሁን እንደ ቅርጫ ስጋ እየተቀራመቷት ነው:: እርስ በርስ እየተተራመሳችሁ የሃገራችሁንና የሕዝባችሁን የመከራ ጊዜ ካራዘማችሁ፣ በጥቃቅን ያመለካከት ልዩነትና በጎሰኝነት ትእቢት ተወጥራችሁ ትልቁን አገር እንዲጠፋ ምክንያት ከሆናችሁ፣የናንተ አላማ ከባንዳዎቹ ኣላማ በምን ይለያል?

አገሪቱ በምቀኝነታችሁ የተነሳ ለናንተም ለእህት ወንድሞቻችሁም ሳትሆን እንዲሁ ተከፋፍላ፣ ወድማ፣ ጠፍታ እንደትቀር በተሸረበ ሴራ ስትመዘበር እያያችሁ ዝም ብላችሁ በእልህና በምቀኝነት ከምትነዱ ምናለ ደህናውን ነገር ቢያሳያችሁ? ምናለበት ባመለካከትና በጎሳ ተከፋፍላችሁ እህት ወንድሞቻችሁን በጥላቻ እያገለላችሁ በመናቆር የሕዝቡን የመከራ ዘመን ከምታራዝሙ ይልቅ የሰው ልጅ ጠላት የሆኑትን ድሕነትን፣ ድንቁርናን፣ ችግርን፣ ረሃብን፣ ምቀኝነትን ለማጥፋት ብትተባበሩ? ከኛ ይለያሉ የምትሏቸውን የሃገራችሁን ልጆች በጥላቻ ከመመልከትና ከማግለል ይልቅ ተባብራችሁ የጋራ ጠላታችሁን ብታስወግዱ፣ የሰው ልጅ ጠንቅ የሆኑት ችግሮች ላይ አተኩራችሁ ለሥራ፣ ለትብብር፣ ለፍቅር፣ ለጋራ እድገት፣ ለእህትማማችነትና ለወንድማማችነት ብትሰለፉ የት በደረሳችሁ፡፡

ያለፉት እናቶችና አባቶች ከዚህ በፊት አደረሱ ለሚባለው ጥፋት እነሱንና ጊዜያቸውን ተጠያቂ አድርጎ ከታሪክ አየተማሩ ያለፈውን ጥፋት ላለመድገም ጥረት በማድረግ ፋንታ አፀፋውን ላሁኑ ትውልድ ካለፈው ጥፋት በከፋ ሁኔታ ለመመለስ ከምትሯሯጡ፣ የሰውን ልጅ እኩልነት አምናችሁ ለነፃነት፣ ለእኩልነት፣ ለመልካም አስተዳደር ማንንም በዘሩ፣ በሃይማኖቱ፣ በጎጡ፣ በፆታው፣ በሰፈሩ ሳትለዩ አመቺ ሁኔታ ብትፈጥሩ እናንተም ሳትበረግጉ ለመኖር ትችሉ ነበር፡፡ ለልጆቻችሁም በሰላም የሚኖሩባት አገር ትተውላቸው ነበር፡፡ እናንተ ግን ክፉዎች የቃየል ደቀመዝሙሮች ናችሁና በእብሪትና በቂም በቀል ተገፋፍታችሁ፣ የዛሬን ድሎት፣ ጉራ፣ ክብርና የቂም በቀል ጥማት ማርኪያ አጋጣሚ አይታችሁ

ተስገበገባችሁ፣ እንደ እብድ ውሾችም ተልከሰከሳችሁ፡፡ ሃያ አምስት አመታት ሙሉ በወገንተኝነት ተከፋፍላችሁ አገሪቱን ድራሿን ለማጥፋትና ለማስጠፋት ስትልመጠመጡ ጊዜ እያለፈባችሁ መሆኑ ሳይገባችሁ እስካሁን ዘለቃችሁ፡፡

ዓለም ባንድነት ካልተሰለፈችና ዓለምአቀፍ ችግሮችን በጋራ ካልተወጣች የሰው ልጆች የወደፊት እጣ ፈንታ አሰከፊ እንደሚሆን በሚለፈፍበት ዘመን ዘርና ጎሳ እየቆጠራችሁ የኔ አያት ባንቺ ወይም ባንተ አያት ተበድሏል፣ ስለዚህ አሁን ደግሞ አያቶቻችሁን በድለዋል የምትሏቸውን ሰዎች የልጅ ልጆች በማግለል እነሱን ለመጉዳት አገር ስታደሙና ቂም በቀል መወጣት የኛ ተራ ነው በማለት የሃሙራቢን ሕግ በዚህ ክፍለ ዘመን ለማሳካት ስትሯሯጡ አታፍሩም? በትምክህት የተወጠራችሁትስ አሁንም በቀድሞው መንፈስ ሌላውን እየናቅን፣ እያንኳጠጥንና እየበደልን እንቀጥል ስትሉ፣ ወይም ከኛ ሌላ ላመራር የተቀባ የለም ስትሉ አታፍሩም? በትምክህት ወይንም በዝቅተኝነት መርዝ ሰክራችሁ ወደ እውነተኛ ዲሞክራሲ ጎዳና የሚያሰኬድ መንገድ ከመቀየስ ይልቅ የጎሳችሁን ወይም የቡድናችሁን የበላይነት ለማስከበር ስታታልሉ፣ ስትዋሹ፣ ታሪክን ለናንተ አላማ በሚመች ሁኔታ ስትጠመዝዙ፣ አገርና ወገንን ስትሸጡ፣ ራሳችሁን በሚያስተዛዝብ ቅሌትና ውሸት ስታዋርዱ፣ ሕብረተሰቡን በችግርና በብጥብጥ ስታንገላቱ አታፍሩም? ቂም በቀል ውጤቱ መጠፋፋት መሆኑ አይገባችሁም? ዳሩ እናንተ በእኩይነትና በእንከፍነት ህመም ተበክላችሁ አገር ለማጥፋት ስለወሰናችሁ፣ እግዚአብሄር የምትመኘውን ንገረኝና ላንተ የማደርግልህን ለጎረቤቶችህ በእጥፍ አደርግላቸዋለሁ ቢለው፣ ‹‹ነገሩ እንደሱ ከሆነ አንድ አይኔን አጥፋልኝ››፣ እንዳለው እርጉም ከናንተ ወገን ያልሆነ ነው ብላችሁ የምታምኑትን ሁሉ ሁለቱም አይኖቹ እንዲጠፉ ምኞታችሁ እንደሆነ ሥራችሁ ይመሰክራል፡፡ በእኩልነት፣ በፍቅርና በመተሳሰብ ጎዳና ብትሄዱ ሃገሪቱ ለሁላችንም ትበቃ ነበር፡፡ እናንተ ግን ስግብግቦች፣ እርጉሞች፣ ምቀኞች፣ ሆዳሞች፣ ወራዶች ናችሁና ለመጠፋፋት ተግታችሁ ምኑም ሳይሳካላችሁ ስትተረማመሱ ትታያላችሁ፡፡ ሃያ- አምስት አመታት እንደ ዋዛ ድሃውን ሕዝብ ማገዶ እያረጋችሁ ዘለቃችሁ፣ ይሄው አሁንም አልበቃችሁ፡፡

መቼም ጥሎባችሁ እርኩሶች ስለሆናች ምክር፣ ተግሳጽ፤ ገንቢ ትችት አይዋጥላችሁም፡፡ ሲነግሯችሁ፤ እንዴ በዚህ ጽሁፍ አቅራቢ የተላለፈው መልእክት ምናልባት ቁም ነገር ሊኖረው ይችል ይሆናል እኮ? በማለት ፋንታ ቺንቅላታችሁ ጥላቻን የመፈልፈል ባሕሪ ስለተጠናወተው ተራ አሉባልታ ማሰራጨት፣ በሃሳባችሁ ያልተስማማውን እንዳይድን አድርጎ ማዋረድ፣ የተነሳው ነጥብ ላይ በማተኮር ፋንታ ሃሳቡን ያካፈለው ግለሰብ የግል ህይወት ውስጥ ገብቶ በመፈትፈት ሃሳቡን ሳትመረምሩ ጉዳዩን ያፈለቀውን ሰው ስብእና ማርመጥመጥ ይቀናችኋል፡፡ አይቼ አይቼ ከናንተ ከክፋት፣ ከእርጉምነት፣ ከምቀኝነት፣ ከዋሾነት፣ ካስመሳይነት፣ ከሆዳምነት፣ ከእርኩስነት፤ ከወኔ ቢስ ቅልስልስነትና ተላካፊ ውሻነት ሌላ ምንም መጠበቅ እንደማይቻል ተገንዝቤ ስለሰለቻችሁኝ፣ ስለበቃችሁኝ፣ ተስፋ የማይጣልባችሁ አጋሰሶች ስለሆናችሁብኝ እነዚህን ቃላት--እኩይና እንከፍን--ለመጠቀም ተገደድኩ፡፡

እነማን ይሆኑ እንዲህ የተባሉት ትሉ ይሆናል፤ አንዳንዶቻችሁ፡፡ ስህተት መስራት መቻላችሁን አለማመን፣ አመጣጣችሁንና ማንነታችሁን አለማወቅ፣ ራሳችሁን ምንም ሳትሰሩ ማጋነን ልማዳችሁ ነውና እኛን አይመለከትም ብላችሁ ይህን ጽሁፍ ሳታልፉት አትቀሩም መቼም፡፡ ለእናንተ ነው የተፃፋው ለሁላችሁም እንደእናንተ ዘርና ወገን ሳይለይ ባጠቃላይ ምሁር ነን ብላችሁ በጥራዝ ነጠቅነት አገር ለምታተራምሱት፣ የስልጣን ጥማችሁ ካልረካ አገር እንድትወድም ሌት ከቀን ለምታልሙት፣ የመጠፋፋት አባዜ ለሚያቅበዘብዛችሁ፣ የፍቅር ወሬ ለሚያስደነብራችሁ፣ ሕዝብን ከማቀራረብ ይልቅ ልዩነትን ማግነን ለሚቀናችሁ በምስራቅ አፍሪካ ቀንድ አካባቢ ተፈጥራችሁ ፈጣሪ ባርኮ የሰጣችሁን የህይወት ፀጋ፣ የተፈጥሮ ሃብትና ጥሩ ያየር ንብረት በቅጡ መጠቀም አቅቷችሁ በምቀኝነት ነገር እያመነዠካችሁና የጥላቻ አተላ እየተፋችሁ በየምክንያቱ ተከፋፍላችሁ ወገኖቻችሁን ለድኅነት፣ ለኋላቀርነት፣ ለበሽታ፣ ለረሃብ፣ ለስቃይ፣ ለስደት ወዘተ…እያጋለጣችሁ የግል የቂም በቀል ፍላጎታችሁን፣ የምቀኝነት መርዝ የመርጨት ሱሳችሁን፣ የቁሳቁስ ጥማታችሁንና፣ ሥጋዊ ፍላጎታችሁን ላስቀደማችሁ፣ አይን እያላችሁ ማየት ለተሳናችሁ ደንባራ አእምሮ ቢሶች፡፡

ክፋትን፣ እብሪትን፣ምቀኝነትን፣ሆዳምነትን፣አድርባይነትን፣ግብዝነትን፣ ጅልነትን፣ዋጋ ቢስነትን፣ታጥቦ ጭቃነትን እንደ ቁም ነገር የሙጥኝ ይዛችሁ በመደጋገፍ፣ በመተባበር፣ በመደማመጥ፣ በመዋደድና በመተሳሰብ ፋንታ አገራችሁንና ራሳችሁን ለከፋ አደጋና ለውጭ ገፋፊዎች አሳልፋችሁ እየሸጣችሁ በእብሪት ለምትደነፉ አጋሰሶች፡፡ ሀፍረት የሚባል መቼም አልፈጠረባችሁ፣ እብሪታችሁ ገደብ የለውም፣ ስተዋሹ አይን የላችሁም፣ ከጥፋታችሁ አትማሩም፡፡ እውቀት ከክፋት፣ ከእብሪተኝነት፣ ከአጉል ትምክህት፣ ከጠባብነት ሊያላቅቃችሁ ሲገባ እናንተ እውቀትን በክፋት፣ በውድመት፣በጥፋት፣ በውሸት፣ በምቀኝነት፣ በእብሪተኝነት ለወጣችሁት፡፡ አወቅን ብላችሁ ሕዝብን ናቃችሁ፣ አወቅን ብላችሁ አገርን ከዳችሁ፣ አወቅን

ብላችሁ ያለፈውንና የወደፊቱን ሳታመዛዝኑ አገር ሸጣችሁ፣አወቅን ብላችሁ አገር ከፋፈላችሁ፣አወቅን ብላችሁ በደል እያያችሁ በቂም በቀል ተገፋፍታችሁ በወገኖቻችሁ ላይ በሃሰት መሰከራችሁ፡፡ ይህ አይነቱ ድርጊት ከእውነተኛ ድንቁርናና፣ ከምቀኛነት፣ ከእኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል ባይ ወደል አህያነት የሚመነጭ እንጂ እውቀትን ገብይቻለሁ ከሚል በአምላክ አምሳል ከተፈጠረ የሰው ልጅ የሚመጣ አይደለም፡፡

የተልከሰከሰ፣ በእርኩስነት የተለከፈ ኋላ ቀር አስተሳሰብ ያፈናችሁ፣ የሰውን ልጅ ማንነት በእርሱነቱና በስነልቦናው ሳይሆን በቋንቋውና በዘሩ የምትለኩ ጊዜ ያለፈባችሁ ምቀኞች ናችሁ፡፡ ሆዳችሁ ሞልቶም አልጠገባችሁ፣ ኪሳችሁ በዶላር ተወጥሮም አልበቃችሁ፣ በሙስናና ራስን በመሸጥ የተከማቸው ሃብትና ንብረታችሁ ተትረፍርፎም አልጠረቃችሁ፣ በደሉን ከምትሿቸው የባሰ የቂም በቀል እርምጃ በመውሰድ ብዙሀንን አፈር ድሜ አስግጣችሁም አልረካችሁ፡፡ ያለፉትን እየወቀሳችሁ ካለፉት በባሰ ሁኔታ ምዝበራን፣ ልዩነትን፣ ጥላቻንና መከፋፈልን እንደ ቁምነገር ስትዘሩ ምንም የማይሰማችሁ ተማርን የምትሉ፣ ነገር ግን አዙሮ ማስተዋል ያቃታቸሁ አውቆ አጥፊ ማይሞች ናችሁ፡፡ ለልጆቻችሁ ሰላምና ፍቅርን ከማውረስ ይልቅ ክፋትን እያወረሳችሁና እርጉምነትን እያስተማራችሁ አገሪቱን ወደማያልቅ የእርስ በርስ ጥላቻና መተራመስ እንደምትመሯት እያወቃችሁ በያዛችሁት የክፋት መንገድ ስትቀጥሉ ምንም አይሰማችሁ፡፡ በምን የተነሳ እንዲህ እንደደነዘዛችሁ ፈጣሪ ይወቅ! ምቀኝነትም፣ ቂም በቀልም፣ ክፋትም፣ እርጉምነትም በእውቀት ሃይል መክሰም ይችሉ ነበር፣ የናንተ ግን የተለየ የዲያቢሎስ ልክፍት፣ ያውም የዳፍንታሙ ዲያቢሎስ ልክፍት ሊባል ይችል እንደሆነ ነው እንጂ በተለመደው መንገድ ለማስረዳት የከበደ እንቆቅልሽ ነው፡፡

አገራችንንና ወገኖቻችንን ጠላቶቻችን እንደሚፈልጉት በዘርና በሃየማኖት ሳንለይ እንወዳለን የምንል ሁሉ፣ ኢትዮጵያ ላይ ላለፉት ሃያ አምስት አመታት ያለማቋረጥ የተሰነዘረው የእኩዮችና የእንከፎች የጥፋት ጥቃት ሊሰማን፣ ሊያንገበግበንና ሊያበሳጨን ይገባል፡፡ ኢትዮጵያ በምን አይነት አሳሳቢ ሁኔታ ውስጥ እንዳለች ተገንዝበን ይህን ጥቃት የመከላከል ኃላፊነታችንን ለመወጣት እየተሳሰብን መተባበር ካልቻልን ሃገራችንን ብቻ ሳይሆን ራሳችንንም እናጣለን፡፡ ‹‹ሃገር የሞተ እንደሆን ወዴት ይደረሳል›› የሚለው አባባል በሁሉም መልክ አገርን ማጣት ጉዳቱ ከፍተኛ መሆኑን ያሰረዳል፡፡ አሜሪካና አውሮፓ መሰደድ ቢቻል እንኳን እሱነቱን ያጣ ግለሰብም ሆነ ሕብረተሰብ የትም ቢሄድ የተሟላ ሰውነት ሊኖረው እንደማይችል መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ሃገራቸውን ያጡ ሰዎች መለያ በማጣታቸው፣ በመዋረዳቸው፣ በመገለላቸውና እነሱነታቸውን እንዲረሱ በመገደዳቸው ጉድለት እየተሰማቸው ራሳቸውን ከሌሎች ዝቅ አድርገው ጥቃትን እየቻሉ መኖር ይገደዳሉ፡፡ በዚህም የተነሳ የህሊና እረፍት እንዳጡ ሲንከራተቱ ኖረው ያልፋሉ፡፡ አገራችንና ሕዝባችን ተንቀዋል፣ ተዋርደዋል፣ ተደፍረዋል፣ ያለ ኃፍረት ተመዝብረዋል፡፡ ለረዥም አመታት በቅን መንፈስ በወንድምነትና በእህትነት መንፈስ ተባብረን እንኳን ሌት ከቀን ያለማቋረጥ ብንለፋ ለማስተካከል በጣም ከባድ ሊሆኑብን የሚችሉ ማሕበራዊ፣ አኮኖሚያዊ፣ አካባቢያዊ፣ ሥነምግባራዊና፣ ባሕላዊ ውድመቶች ደርሰውብናል፡፡ ሞራላችን ተሽመድምዷል፣ በራስ የመተማመን ስሜታችንም በሚያሳዝን ሁኔታ ተዳክሟል፡፡ ሕብረተሰባችን ያለ ምንም ማጉረምረም አንገቱን ደፍቶ እንዲገዛ፣ በመሰሪ የምቀኝነት ዘዴ ጠማማ ጠማማውን እንዲከተልና ደህና ደህናውን እንዲንቅ፣ የራሱ የሆነውን ጥሩ ነገር ሁሉ እንዲያንጓጥጥና እንዲጠላ የሚገፋፋ የሕሊና ሰለባ ተካሂዶበታል፡፡ አኩሪ የጋራ ታሪኩንና ያሉትን መልካም ማሕበራዊ፣ባሕላዊና ሥነምግባራዊ እሴቶች እንዲያንቋሽሽ፣ ጎሳውን አግንኖ አገሩን እንዲንቅ፣ እንዲከዳና እንዲያዋርድ፤ የራሱን ማንነት ከሰውነት ይልቅ በጎጥ መነጽር እንዲያይ ተሸብቦ በጥቃቅን ልዩነቶች በመከፋፈል ለምዝበራ አገዛዝ እንዲመች ተዘጋጅቷል፡፡

ሕዝቡ ትልቁን ሃገርን የመውደድ፣ የማክበር፣ የማስከበር፣ የመጠበቅ፣ የማልማትና የማጎልበት ሃላፊነቱን ዘንግቶ በጥቃቅን ልዩነቶች ላይ በማተኮር እየተናቆረ ሃገሩን ለአገር አጥፊዎች መፈንጫነት አሳልፎ እንዲሰጥ በተለያየ ሰይጣናዊ ዘዴ ልዩነትን የማግነኑ፣ ነገር የመቆስቆሱና ስሜት የማጋጋሉ ዘመቻ ሳያባራ ቀጥሏል፡፡ ‹‹የአክሱም ሃውልት ለወላይታው ምኑ ነው›› በሚልና በመሳሰሉ የከፋፋይነት ዘዴዎች በመጠቀም ሕዝብ ከሕዝብ እንዲራራቅ፣ እንዲጠላላና እንዳይተባበር የሚያደርጉ እቅዶች በሰፊው ተሰራጭተው ሕዝቡን ከቀዬው ያላለፈ አስተሳሰብ እንዲያቀነቅን አድርገውታል፡፡ እንኳንስ በአክሱም ሃውልቶችና በግብፅ ጊዛ ከሚገኙት ፒራሚዶች ጀምሮ እስከ ማዳጋስካር ድረስ የኢትዮጵያ ሰዎች አሻራ ሊኖር መቻሉን አለመጠርጠር የተፈጥሮ ክስተትንና የታሪክ እውነታዎችን መፈታተን ነው፡፡ የሰው ልጆች ታሪክ፣ አመጣጥና የዘር ግንድ በዛሬ መነፅር ብቻ መታየት አለበት ብለው ራሳቸውን ያሳመኑ ሰዎች ለእውቀትም ሆነ ለጥበብ ቦታ እንደማይሰጡ ግልፅ ነው፡፡ ሁኔታዎችን ለራሳቸው አኩይ አላማ በሚጥቅም መንገድ እያቆላመሙ ከትብብር ይልቅ ልዩነትን እያገነኑ መዝለቅ እንደሚፈልጉ አገራችን ላይ እየሰሩ የሚገኙት የማጋጨት ዘመቻ በግልጽ ያስረዳል፡፡

እንደዚህ አይነቱ ከይሲ አካሄድ ለሀገሪቱ አንድነትና እድገት ጠንቅ ነው፤ ላገር የሚጠቅም፣ የሕዝብን ፍላጎት የሚያንጸባርቅ መንገድ ይቀየስ እያሉ የሚወተውቱ እህቶቻችንና ወንድሞቻችን ላይ የሚፈጸመው ኃፍረት የለሽ በደል ሊያናድደን፣ ሊሰማን፣ ሊቆረቁረን ይገባ ነበር፡፡ ዳሩ ወኔው የተሰለበ፣ ከጥቅሙ ሌላ ምንም አይነት በጎ ነገር የማይታየው፣ የእንስሳ ባሕሪ የተላበሰ ሕብረተሰብ እንዲፈጠር እየተደረገ ስለሆነ ያገሪቱ መውደምና የሕዝቡ መበደል የሚቆረቁራቸውና የሚያሳስባቸው እያነሱ፣ ተገዢነትን ያለምንም ጥያቄ የተቀበሉ፣ በተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ተደልለው የደነዘዙ የቁም ሙቶች (ዞምቢዎች) እየበዙ ነው:: ብዙ ተብሏል፣ ብዙ ተፅፏል፣ ብዙ ተለፍቷል፤ ወጤት ግን አልታየም፡፡ በኔ በኩል ነገሮች ለማይገባቸው ወይንም አውቀው ለሚያጠፉ መሰሪዎች የጥፋታቸውን ገደብ ማጣት ሊያሳውቃቸው በሚችልና ከነሱ የንቀት ድንፋታ ጋር በሚመጣጠን ቋንቋና ተግባር ማነጋገር ነው ያለው አማራጭ ባይ ነኝ፡፡ ይህም ስለተደረገ ይገባቸዋል ማለት አይደለም፡፡ ክፉዎች፣ እርኩሶች፣ ግትሮች፣ እርጉሞች፣ ሆዳሞች፣ እብሪተኞች ናቸውና! እነሱን ማባበሉ ግን ሊበቃ ይገባዋል፡፡ ሌባ፣ ቀማኛ፣ ቂመኛ፣ ምቀኛ፣ ዘረኛ፣ ሆዳም፣ አስመሳይ፣ ውሸታም፣ አገር አጥፊ ባጠቃላይ እኩይነትና እንከፍነት የተጠናወተው ቡድንም ሆነ ግለሰብ ቃላት ሊቆጠብለት አይገባም፡፡ እነሱ የኛን ቅስም ለመስበርና ሃገራችንን ለማጥፋት ያልተጠቀሙበት መሳሪያ የለምና! የጥፋታቸውን አስከፊነት ቃላትን በማለዘብ ልናለሰልስላቸው አይገባም፡፡

ልምምጥ፣ አንገት መድፋት፣ አገራችንንና፣ እህት ወንድሞቻችንን ቅጥ ባጣ እብሪት ንቀው ለሚበድሉና እኛነታችንን ለሚያጠፉ እኩዮች ተጨማሪ አድል የመስጠት ትዕግስቱ ሊያበቃ ይገባዋል፡፡ በቃ! በቃ! በቃ! የሚሰማንን በቃላት ተርጉመን ሃሳባችንን በማካፈል ሕብረተሰቡን ለመብቱ እንዲነሳሳ ማነቃቃቱን እስከመጨረሻው መተው የለብንም፡፡ ከዚህ አልፈንም ነፃነታችንን ማስመለስና ራሳችንን በምንፈልጋቸውና በሚወክሉን መሪዎች የማስተዳደር መብት በግድም ሆነ በውድ የራሳችን የማድረግ ድፍረቱና ተነሳሽነቱ ሊኖረን ይገባል፡፡ የሚፈለገው ቀስ በቀስ ሁላችንንም በተስፋ መቁረጥ አንገታችንን አስደፍቶና አፋችንን አስይዞ ቋሚ ተገዢ ማድረግ ነውና!

እዚህ ላይ ልንገነዘብ የሚገባን ነገር ሃገራችን የዝግምታ ሞት እየሞተች መሆኑን ነው፡፡ የሕወሃት እኩዮች ሀገሪቱን በጎሳ የመገነጣጠል አላማቸው እስካሁን በፈለጉትና ባለሙት መንገድ ባይሳካላቸውም፤ በመሃከላችን እየቀበሩት የሚገኘው የዘር፣ የሃይማኖትና እርስ በርስ የመናናቅ መርዝ ጊዜውን እየጠበቀ እንደ ነቀርሳ በመሰርሰር አንድነታችንንና አብሮነታችንን እየተፈታተነው ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የህብረተሰባችንን፣ በተለይም የወጣቱን የሀገር ፍቅር ስሜት በተለያየ የማማለያ ዘዴ በመስለብ የሚካሄደው የስነ ልቦና ቡርቦራ አገራችን ምንም እንኳን የግዛት አንድነቷ እንደተጠበቀ ያለ ቢመስልም፤ ሀገርን ለማልማትና ሕብረተሰቡን ከድህነት አረንቋ ለማውጣት በተቀዳሚነት የሚያስፈልጉት ትብብር፣ መተሳሰብ፣ ሃገራዊ ስሜት፣ የኢትዮጵያዊነትና የወገን ፍቅር እየጠፉ ስለሆነ አብረን ሆነንም በልባችን ስለተለያየንና እንድንጠላላ ስለተደረገ ባንድ መንፈስ አገራችንን ከክፉ አስተዳደር፣ ከድህነትና ከኋላ ቀርነት አላቅቆ ወደተሻለ አስተዳደር ለማሸጋገር የሚያዳግት ሁኔታ ውስጥ በግድ የተዘፈቅን መሆኑን ልንረዳው ይገባል፡፡ በዚህ ሁኔታ በፈጠሩት ክፍተት በመጠቀም ዘረኞች፣ ጎጠኞች፣ ሆዳሞች፣ ቂም በቀለኞች፣ ቀናተኞች፣ ምቀኞችና መዝባሪዎች ሃገራችንን እንደፈለጉ እያተራመሷት ይገኛሉ፡፡

ሃገራችን እየተጓዘችበት ያለው መንገድ ለሕልውናዋ አደገኛና ጠማማ ጎዳና ነው፡፡ ለሕዝቧ ሳይሆን የሚጠቅመው ለዘመናዊ ባንዳ ባላባቶችና በእድገት ስም ምዝበራን ለሚያሰፋፉት የውጭ ሃይሎች ነው፡፡

የሃገሪቱን ሕዝብ የጥቂቶች ተገዢ የሚያደርግ፣ ቅርስና ሃብቷን በባእዳን የሚያስመዘብር፣ በእውነተኛ ዲሞክራሲ ፋንታ በዲሞክራሲ ስም ያንድን ጠባብና ቂመኛ ቡድን አምባገነናዊ አገዛዝ የሚያጠናክር ብልሹ የጥፋት ጉዞ ለመሆኑ ባሳለፍናቸው አመታት የተከናወኑት ይሉኝታ አልባ የፖለቲካ ውሳኔዎችና፣ ገደብ የለሽ ኢኮኖሚያዊ ዘረፋዎች ይመሰክራሉ፡፡ ሃገራችን እየወደመች፣ ብሩሕ ተስፋዋ እየጨለመ፣ የሕዝቧ ስነምግባርእየበከተ፣ ሃብቷና ንብረቷ በማይጠረቁ መዥገሮች እየተመጠጠ፣ ወገኖቻችን እየተበደሉ፣ እየተንከራተቱ፣ የበይ ተመልካች እየሆኑ እየተጎሳቆሉና እየተሰደዱ ማየት ሊያንገፈግፈን ይገባል፡፡ የወደፊት ተስፋችንን እያደበዘዘ ክፋትን ስንቁ አድርጎ የዘመተብን መሰሪ አገዛዝ የመከፋፈል መርዙን በስፋት ረጭቶ ስለሰራለት ተደላድሎ እየመዘበረን መሆኑን አውቀን ለነፃነጻችን መነሳት ይገባናል፡፡ ጊዜ ሊሰጠው የማይገባ አንገብጋቢና አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ነው ያለነው፡፡

አስኪ ሁኔታውን እንመርምር፡፡ በእውነት ከግል ጥቅም ተገዢነት፣ ከጎጠኝነትና ከምቀኝነት ልጓም ወጥተን ብንመለከተው ኢትዮጵያችን ባለፉት ሃያ-አምስት አመታት ሊኖራት የሚገባው አስተዳደር አሁን የምናየው አይነት ለሕዝብም ሆነ ላገር ምንም አይነት ክብርም ሆነ ፍቅር የሌለው አምባ ገነንነት መሆን ነበረበት? የእድገቷስ ደረጃ አሁን ባለው ሁኔታ በሌሎች መጠቀሚያነትና ሸቀጥ ማራገፊያነት መወሰን ይገባው ነበር? ሕዝቧ ከረጅም አመታት መስዋዕትነት በኋላ አሁንም ለበይ ተመልካችነት፣ ለከፋ ድሕነት፣ ለስደት፣ ለእርዛት፣ ለረሃብ፤ ለነፃነት ጥማት መጋለጥ ይገባው ነበር? ለመላው ዓለም፣ በተለይም ለአፍሪካ፤ ራስን

የማክበርን፣ በራስ የመተማመንን፣ የጀግንነትን፣ ተባብሮ ጠላትን የመመከትን ጥበብ ያስቀሰመ ሕዝብ ዛሬ ተከፋፍሎ ራሱን በማዋረድ የባእዳን የእጅ አዙር ቅኝ ተገዢና ገባሪ ሆኗል፡፡ ሕዝቡ ባገሩ ላይ የበይ ተመልካች እንዲሆን አገሪቱ ያስተማረቻቸው ልጆቿ የራሳቸውን፣ የወገኖቻቸውን፣ የልጆቻቸውንና ያገራቸውን የወደፊት እጣ ፈንታ መመለሻ ወደሌለው አዘቅት በምቀኝነት፣ በግብዝነት፣ በሆዳምነት፣ በዘረኝነትና በግትርነት እየመሩት ይገኛሉ፡፡

ክፋትና ምቀኝነትን ሰንቀው የመጡ ተራ ወንበዴዎች ለሃያ አምስት አመታት ሕዝቡን በጠመንጃ በመመካት ቀፍድደው አስረው በባእዳን ምንደኞችና በሆዳም ያገር ውስጥ ዘረኞች፣ ትምክህተኞችና የዝቅተኝነት ስሜት ጥፋትን ብቻ በሚያስመለክታቸው የመንፈስ ድውዮች አገሪቱን እያስመዘብሩ ናቸው፡፡ አልፈው ተርፈውም ለምኞት ስንል ባርነትን የምንመርጥ ይመስል እድገት አምጥተንላችኋል ይሉናል፤ እኛን እየጠሉ የሃገራችን ሃብት አማኧቸው የመጡበትን የመገንጠል አላማ ወደጎን አስቀምጠው በጉልበት እንምራችሁ የሚሉን ተራ አታላዮች፡፡ ይሉኝታና ኃፍረት የሚባል ነገር ምን እንደሆነ የማያውቁ፣ እንደ ምስጥ አገር የሚቦረቡሩ፣ እንደመዥገር ደም የሚመጡ፣ በምቀኝነትና በግትርነት እየተቅበዘበዙ አገሪቱ የነበራትን ጥሩ ነገር ሁሉ ለማውደም ቆርጠው የተነሱ እርኩሶች ገጠሟት ይህችን የምታሳዝን አገር፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶቹና ምቀኞቹ ስለበዙ፣ የውስጥ ቦርቧሪዎችም እንደ አሸን ስለፈሉበት፣ ራሱን በድሎ ያስተማራቸውም ውለታ ቢስ ምሁር ነን ባዮች የትልቋን አገር እጣ በመንደር፣ በሰፈርና በጎጥ ራእይ ስላጠበቡት ማንም ሕዝብ በዚህ ዘመን ሊቀበለው የማይገባውን አገዛዝ አንገቱን ደፍቶ እንዲቀበል አስገደዱት፡፡  እስቲ ተጠየቁ እናንተም በእኩዮቹ ወገን ተሰልፋችሁ አገራችሁን፣ ሕዝባችሁን፣ ታሪካችሁን ከድታችሁ ለጠባብ ጎሰኝነትና ለጥቅማችሁ የምታጫፍሩ የአእምሮ ሰንካሎች፡፡ ሃገሪቱን የምቀኝነት፣ እርስ በርስ የመጠፋፋት፣ የመናናቅ፣ የክፋት፣ የድህነት፣ የስደት፣ የልመና፣ የዘመናዊ ባርነት መናኸሪያ አደረጋችኋት፡፡

ባለፉት ሃያ-አምስት አመታት በቅን መንፈስ፣ በመተሳሰብ፣ በፍቅር ብትተባበሩ፣ ለእውነተኛ ነፃ ምርጫ፣ ዲሞክራሲን ለማስከበር ለሚረዱ እውነተኛ ተቋሞች ግንባታ፣ ለሰላማዊ ሽግግርና ራስ አስተዳደር ሕዝቡን ብታዘጋጁት፤ ለራሳችሁ የመንፈስ እረፍትና እርካታ፣ ላገራችሁ መልካም ተስፋ፣ ለሁሉም ወገኖቻችሁ እድገትና ብልፅግና፣ ለልጆቻችሁ ዘላቂ ሰላምን ማረጋገጥ ስትችሉ፤ ክፋት፣ እርጉምነት፣ መሰሪነት ከእግር አስከ ራሳችሁ ወጥረው ስለያዟችሁ ኢትዮጵያ በሚለው ማእቀፍ ውስጥ ምንም አይነት ቅንና መልካም ነገር ሊታያችሁ አልቻለም፡፡ ገንቢ ምክር የሚለግሷችሁን መናቅ፣ ማንጓጠጥ፣ ማዋረድ፣ ማሳጣት፣ ማጉላላት፣ ማሰር ማንገላታትና መግደል ሆነ ምላሻችሁ፡፡  እንዴት እኛን የመሰልን ‹‹ወርቅ›› ፍጡራን እንደፈራለን፣ አመራራችንስ እንዴት ተብሎ ጥያቄ ውስጥ ይገባል፣ ማንስ ምድራዊ ኃይል ሊፈታተነን፣ ሊጠይቀን፣ ሊያስገድደን ጉልበቱና ችሎታው ሊኖረው ይችላል? በሚል ያለፈበት ባላባታዊ አመለካከት እብሪታችሁ ገነነ፡፡ የማትረቡ፣ በልታችሁ የማትጠረቁ፣ ግጣችሁ በቃኝን የማታውቁ፣ የናንተ ያልሆነውን ሰርቃችሁ የምትደነፉ፣ ሰውን መብት አሳጥታችሁ ለምን ተጠየቅን የምትሉ፣ ክፋት እንደቅሪላ ልባችሁን ያሳበጠው ተራ መልቲ አታላዮችና ራሳችሁን የሸጣችሁ ዘመናዊ ባሪያዎች መሆናችሁን አስመሰከራችሁ፡፡  ከታሪክ ለመማር ብቃት ያለው አእምሮ እንደሌላችሁ ተራ የውንብድና ሥራችሁ መሰከረ፡፡ አንጎላችሁ ለሰው ልጅ በተሰጠ አምላካዊ መንፈስ ሳይሆን የሚመራው እንደአጋሰሶች በሞራ በተሞላ አንጎልና እንደ እባብ ለመንደፍ ባቆበቀበ ስነ ልቦና እንደሆነ አረጋገጣችሁ፡፡

እስኪ ተጠየቁ እናንተም በምቀኝነት ተወጥራችሁ በችላ ባይነታችሁ፣ በአያገባኝም ባይነታችሁ፣ በተራ ጅልነታችሁ፣ በነፈዝነታችሁና በጎጠኝነታችሁ አገራችሁንና ወገኖቻቸችሁን ለክፉ እየሰጣችሁ ለምትመፃደቁት እንከፎች፡፡ እህት ወንድሞቻችሁን ለጥቃት እያጋለጣችሁ ሕይወት ሳይሆን ኑሮ ለተመቻችሁ ደንባሮች፡፡  እውነትን ለጥቅምና ለቂም በቀል እየለወጣችሁ በእብሪት፣በምቀኝነተና በራስ ወዳድነት ታጅላችሁ እህቶቻችሁንና ወንድሞቻችሁን ላራጆች አሳልፋችሁ እየሰጣችሁ፤ ያሳደገች፣ ለቁም ነገር ያበቃች አገራችሁን የከዳችሁና በወገናችሁ ላይ በሃሰት የምትመሰክሩ የሀገርና የወገን ደምና ወዝ መጣጭ የተባይ ተባዮች፡፡

ለችግር በወቅቱ መፍትሄ አለመፈለግ ‹‹ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ›› የሚለውን ብሂል ያስታውሳል፡፡ አገር አጥፊዎች ጊዜ ሲሰጣቸው ጥፋታቸው እየጠለቀ፣ ውድመታቸው እያየለ መሄዱ ላገራችን ተማርን ባዮች ሳይገለፅላቸው ቀርቶ ይሆን?  ያገራችን ማህበራዊ፣ አኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና አካባቢያዊ ችግሮች እየሰፉ፣ እየጠለቁና አየተወሳሰቡ መሄዳቸውን፣ በዚህም የተነሳ ሀገራችን ያለችበት የችግር ማጥ እየሰፋ በድህነት፣ በድንቁርናና በረሃብ ላይ ያካባቢ፣ የባህል፣ የስነምግባርና ያስተሳሰብ ብክለት እየመረዛት፣ የቅን መንፈስ እጥረት ወደ ኋላ እየጎተታት፣ የመከፋፈልና የመናናቅ አባዜ እያሽመደመዳት፣ የወገንተኝነት አመርቃዥ ደዌ እየበከላት፣  የአድር ባይነት ልፍስፍስ መንፈስ አያጨመላለቃት፣የእብሪት መግነን እያቀጨጫት መሆኑ

ያሳስባቸው ይሆን? የኛንና የልጆቻችንን እጣ ፈንታ ካላስተካከልነው ለራሳችንም ሆነ ለልጆቻችን የምናወርሰው የምድር ላይ ሲያልን ሊሆን ይችላል ብለው ይጨነቁ ይሆን? ወይስ እንደአጋንንትነታቸው መጠፋፋትን ነው የሚመኙት? የወደፊቷን ኢትዮጵያ እንዴት ያዩዋት ይሆን? ከምድረ ገፅ ጠፍታ በምትኳ በማያባራ የእርስበርስ ግጭት የሚተላለቁ ትናንሽ በጎሳ የተከፋፈሉ የአምባገነኖችና የውጭ መዝባሪዎች መፈንጫ የዝንጀሮ መንግስቶች የሚተራመሱበት አካባቢ?

የሀገር ፍቅር ስሜቱ የተሰለበ፣ ምቀኝነት እንደ ዲያቢሎስ የተጠናወተው፣ እርስ በርሱ የተናናቀ፣ ከውጭ የመጣን ማንኛውንም ነገር እንደጣኦት የሚያመልክ፣ ክፋትና እርስ በርስ መጠላላት እንደ እከክ የወረረው፣ ሥርዐት አልበኝነት ያተራመሰው ሕዝብ መኖሪያ እየተደረገች የምትገኘው አገራችን በጥቂት እርጉም ልጆቿ ተክዳ ዋጋ በሌለው ብልጭልጭ ተኳኩላ ያደገች እንድትመስል እየተደለለች ሕልውናዋ ግን ቀስ በቀስ እየተቦረቦረ ከመጣ በርካታ አመታት አስቆጠረች፡፡ የእድገትና የልማት አቅጣጫዋ በቅጡ ቢቀየስ፣ በሰብአዊ መብት መጠበቅና በሰው ልጅ የእኩልነት መርህ እየተመራ ለሁሉም ሕዝቧ የሚቀረቀር አስተዳደር ብታገኝ፣ ለአፍሪካ የተመጣጠነ ሁለ-ገብ እድገት ምሳሌ የመሆን እድል የነበራት አገር ነበረች፡፡ ፈጣሪ ሁሉን አሟልቶ ሰጥቷት ነበር፡፡ ቅን መንፈስ እንዳይለመልምባት የሚሯሯጡት ከይሲ ሀፍረተ-ቢስ ተማርን ባይ ልጆቿ ግን እርስ በርስ በመናናቅ ለጠላቶቿ በር ከፍተው የወደፊት እድሏን አጨለሙባት እንጂ፡፡

የደርግን መንግሥት ጨካኝ አገዛዝ አሰወግጄ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የተሻለ አመራር አመጣሁ እያለ የሚመፃደቀው ወያኔ/ኢሕአዴግ የተባለው የተራ ወንበዴዎች ቡድን ከስር መሠረቱ በአስተሳሰቡም ሆነ በይዘቱ እንዲሁም በራዕዩ ምንም አይነት ኢትዮጵያዊነት እንደሌለው አስካሁን ያልገባቸው እንከፎች በብዛት አሉ፡፡ ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ ሌላን አምኖ ቢታለል አታላዩን ወቅሶ ከሁኔታው መማር ብልህነት ነው፡፡ ለሁለተኛ፣ ለሶሰተኛና ከዛም በላይ ተመሳሳይ የጥፋት መልዕክትን በተደጋጋሚ ይዞ ለሚመጣ አታላይ ያለማቋረጥ መውደቅ ግን እንከፍነት ነው፡፡ ወያኔ/ኢሕአዴግ ደግሞ ያለማቋረጥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሲያስፈራራ፣ ሲንቅ፣ ሲያሞኝ፣ ሲያታልልና ሲደልል እንደኖረ ድርጊቶቹ ምስክሮች ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ውጭ አገር የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ኢትጵያውያንን በተደጋጋሚ ሲያታልል እያዩ ትምሕርት መቅሰም ያቃታቸው በርካታ ምሁር ነን ባይ የእንከፍ እንከፎች ግን በብዛት ይገኛሉ፡፡ አንዳንዶቹ ተስፋ ቆርጠው በተለመደው የበታችነት ስሜታቸው በኃያላን የተደገፈ መንግሥትን አንጋፋም በማለት ራሳቸውን ሲሸጡ፣ የተቀሩት ደግሞ ስህተት ብናይም የኛን ጎሳ አባላትን ወይንም ከኛ ጋር በጥቅም የተሳሰሩ ሰዎችን ብንቃወም ጥቅማችን ይጓደላል በማለት የነገን ሳይሆን የዛሬን እያዩ እንደ ተባይነታቸው የተገኘውን ሁሉ እያግበሰበሱ ለመዋጥና በተለመደው ተላላፊ የውሸት በሽታቸው ያገኙትን ሁሉ ለመልከፍ ሲቅበዘበዙ ይስተዋላሉ፡፡

አንዳንድ እንከፎች ደግሞ አሜሪካና የውጭ መንግስታት ወያኔ/ኢህአዴግን እስከደገፉት ድረስ አካሄዱ ጥሩ ነው በማለት ዉሃ በፈሰፈሰበት አቅጣጫ እንደሚነጉደው የሞተ አሳ ሌሎች በቀየሱላቸው መሰሪ አቅጣጫ ሲግተለተሉ ይታያሉ፡፡ ቀሰምን የሚሉት እውቀት ላይ ላዩን አየጋለቡ የሚመሰክሩለትን የህንፃ ግንባታና የልመና አኮኖሚ እንጂ በአይናቸው የሚያዩትን ግልፅ የሆነውን አሰቃቂ ድህነት፣ እርዛት፣ የነፃነት ጥማት፣ ግፍ፣ በደል፣አድልዎ፣ ምዝበራና፣ ሃገር የማጥፋት፣ ወገን የመከፋፈልና ባሕልን የማርመጥመጥ ዘመቻውን ሊያሳያቸው አልቻለም፡፡ ለመንፈስ ባርነት ራሳቸውን አዘጋጅተዋልና ችግሩ ምን ግልፅ ቢሆን ማየት ለማይፈልግ እንዴት ሊታይ ይችላል? አልፈው ተርፈውም ጌቶቻቸው ምዕራባውያንና ቻይና የሃገራችንን ጥቅም ያስጠብቁልናል ብለው ሕዝብን ሲያታልሉ ይደመጣሉ፡፡ ለመሆኑ መቼ ነው በታሪክ ውስጥ አሜሪካም ሆነች ሌሎች አገሮች ከራሳቸው ጥቅም ሌላ የሌሎችን ጥቅም ሲያስጠብቁ የታዩት? ከነሱ አላማ ጋር የተስማማውን እየደለሉ ያልተስማማውን ደግሞ በጉልበት እየዳመጡ፣ እያስገደዱና፣ እያስፈራሩ የራሳቸውን ጥቅም ያለምንም ማወላወል ለማስጠበቅ እንደሚሯሯጡ ግልፅ ነው፡፡ ላለመዳመጥ የፈለገ ደግሞ ጠንካራ ሆኖ መገኘት፣ ከሕዝብ ጋር መተባበር፣ ብሔራዊ ጥቅምን ማስቀደም፣ መጠንቀቅና ራስን መቻል ያስፈልገዋል፡፡ የኛ ጉዶች ግን ይህን ከማድረግ ተገዢነትንና ለማኝነትን ለራሳቸውም ለሕዝባቸውም መርጠው አገራቸውንም የሌሎች መጫወቻ፣ የአለም አቀፍ ምዝበራ ቤተ ሙከራና የዘመናዊ ባርነት መናኸሪያ እያደረጓት ይገኛሉ፡፡

ሃገሪቱን የጎበኘ ማንኛውም የውጭ አገር ሰው እንቆቅልሽ የሚሆንበት እንዴት ይህችን የመሰለች በተፈጥሮ ሃብት፣ በአየር ንብረት፣ በታሪክ፣ በባሕል፣በመልክአ ምድራዊ አቀማመጥ የታደለች አገር፤ ለረሃብ፣ ለድህነት፣ ለኋላ ቀርነትና ለስደት ልትጋለጥ ቻለች? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ መልሱ የልጆቿ የቅን መንፈስ እጥረት፣ የምቀኝነት መብዛት፣ እርስ በርስ መናናቅና የመልካም አስተዳደር ጉድለት ለመሆኑ ምንም የሚያጠራጥር ነገር የለውም፡፡

በታሪክ እንዳየነው የውጭ መንግስታት ጥቅም እስካገኙበት ድረስ ከማንም ጋር መወዳጀታቸው የማይቀር ነው፡፡ ይህን እውነታ ተገንዝቦ የራስን ችግር በራስ መንገድ መፍታት ይገባ ነበር፡፡ ሆኖም አገሪቱ ያሰተማረቻቸው የፖለቲካ አመራሩንና ሕዝብን የመምራቱን ሓላፊነት በሁሉም አቅጣጫ የተቆጣጠሩት እኩዮችና እንከፎች በብዛት በራስ የመተማመን ችግር ይታይባቸዋል፡፡ በራሳቸውና በህዝባቸው ከመተማመንና በፈጣሪያቸው ላይ ተስፋ ከመጣል ይልቅ የምእራቡን አለም ያመልካሉ፡፡ ለችግራቸው መፍትሄ እውነተኛ እውቀትን በመጠቀም፣ እውነትን በመሻትና ሕዝብን በማበረታታት ሳይሆን የምእራባውያንን እጅ እየጠበቁ ከነሱ በሚያገኙት የማያዛልቅ ኃይልም ሆነ ገንዘብ በጉራ ይወጠራሉ፡፡ ለዚህም ነው ወያኔ/ኢህአዴግ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲቀበለው ከመመኘትና ከመስራት ይልቅ የምእራባውያንንና የውጭ ኃይሎችን ድጋፍ፣ እርዳታ፣ ጊዜያዊ ፍቅርና መተማመኛ በልምምጥም ሆነ በትእቢት ሲፈልግ የሚታየው፡፡ እነሱም አልነፈጉትም፣ የሚፈልጉትን ጥቅም እስከሰጣቸው ድረስ የሚያስፈልገውን ድጋፍ ሲለግሱት ኖረዋል፣ ወደፊትም የኢትዮጵያ ሕዝብ ካደነዘዘው የመከፋፈል አባዜ ወጥቶ በትብብር መብቱን በውድም ሆነ በግድ የራሱ አስካላደረገ ድረስ ይቀጥሉበታል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት፣ ሰላም፣ እድገት፣ ከድህነት መላቀቅ ለነሱም ሆነ ለወያኔ/ኢሕአዴግ ቅድሚያ የሚሰጣቸው አንገብጋቢ ጉዳዮች አይደሉምና!

ጣሊያን አድዋ ላይ ድል በተመታ በዐርባኛው አመት ለሁለተኛ ጊዜ ኢትዮጵያን ሲወር እንግሊዝና ፈረንሳይ ሙሶሊኒን ለመለማመጥና እነሱ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጫና ለማብረድ ሲሉ ኢትዮጵያን መስዋእት አላደረጉምን? አሁንስ በውሸት ዲሞክራሲ ስም ምእራባውያን ሃገሪቱ ቅጡን ባጣ አምባገነናዊ እብሪት ስትታመስ፣ ለአመታት ሰብአዊ መብት በግልፅ ሲጣስ፣ የሕዝብ ኑሮ ሲመሰቃቀል፣ ዜጎች በአስተሳሰባቸውና በአመለካከታቸው የተነሳ ሲገደሉና ሲጋዙ እያዩ ምን ያደረጉት ተጨባጭ ነገር አለ? የአፍሪካ ቀንድን አካባቢ የጉልበት ሚዛን ለመጠበቅ ሲባልና ሀገሪቱ ላይ የሚታየው ምዝበራ ላይ ያተኮረ ዘላቂነት የሌለው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ለነሱ የሚሰጠው ጥቅም እንዳይስተጓጎል የኢትዮጵያ ሕዝብና ኢትዮጵያ የምትባለውን ሃገር አሳልፈው ሸጠው የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ እየተሯሯጡ አይደለምን? በዚህ ላይ የሃያልነት እብሪት አያቆጠቆጠ የሚገኝባቸው ቻይናንና ሕንድን የመሳሰሉት ሀገሮች ስለኢትዮጵያ ሲያስቡ የሚታያቸው ጥቅማቸውን የሚየስከብርላቸው መንግስት መኖሩ እንጂ ዲሞክራሲ መስፈኑ፣ ሕዝቡ በኑሮው መርካቱና ሃገሪቱ በእውነተኛ የእድገት ጎዳና ላይ መሆኗ መቼ ሆኖ ያውቃል?

ከሁኔታው እንደምንረዳው ብሔራዊ ጥቅሙን የሚያስጠብቅ መንግሥት ለባእዳን ባለመመቸቱ አይበረታታም፡፡ ስለዚህም አፍሪካ ውስጥ እንዲኖር አይፈለግም፡፡ ወያኔ/ኢሕአዴግም በተቀነባበረ ዘዴ ስልጣን ላይ እንዲወጣ የተደረገው የከሀዲነት፣ የባንዳነት፣ የከፋፋይነት፣ የአስመዝባሪነትና የሆዳምነት ባሕሪው ምእራባውያን በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ለሚፈልጉት፣ በነሱ መመዘኛ ‹‹የተረጋጋ›› ሁኔታ ፈጣሪና የነሱን ጥቅም አስጠባቂ እንደሚሆን ስለተረዱ ነው፡፡ አሁን እያደረጉ ያሉትም ይህን ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ያለማሰለስ የሚሰራላቸውን የወንበዴ ቡድን በተገኘው ሁሉ መንገድ እየደገጋገፉ ያልፈጠረበትን እነሱ ‹‹ወጣት ዲሞክራሲ›› የሚሉትን ለኢትዮጵያውያን ግን ‹‹ጭራቅ ዲሞክራሲ›› የሆነባቸውንና እድሜው እየገፋ ሲሄድ አደብ በመግዛት ፋንታ እርጉምነቱ፣ ግትርነቱ፣ ይሉኝታ ቢስነቱና ትእቢቱ እየባሰ የሚሄደውን ከምንም የከፋ አምባገነንነት የሚያበረታቱት፡፡

ለዚህም ነው አፍሪካ ውስጥ በጣት የሚቆጠሩ እውነተኛ ዲሞክራሲዎች ያሉት፡፡ እነሱም በከፍተኛ የምእራባውያን ተፅእኖ ውስጥ ናቸው፡፡ በኢኮኖሚ፣ በውጭ ጉዳይ፣ በደህንነት ጉዳዮች ላይ የምእራቡ አለም ጥቅም እስካልተጠበቀ ድረስ ያገሬ ጥቅም ይበልጥብኛልና የልማት መስመሬን ለሕዝቤ በሚመች አቅጣጫ ነው የምመራው ብሎ የሚከር መንግስት እንዳይኖር በተለያየ ዘዴ የማደናቀፍ ተግባር ሲካሄድ ይታያል:: እነሱ የሚፈልጉትን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጥቅም የሚያስጠብቅ መንግስት ግን በሁሉም አቅጣጫ እርዳታና ማበረታታት ይደረግለታል፡፡

በዚህ መልክ የወያኔ/ኢህአዴግ መንግሥት በኢትዮጵያውያን፣ ለኢትዮጵያውን የተቋቋመ መንግሥት ተደርጎ እንዲታሰብ፣ አለምአቀፍ ተቀባይነትም እንዲያገኝ ለማድረግ የኢትየጵያ ወዳጅ ነን ባይ ጠላቶች ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ እንዲረዳቸው ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ነው፡፡ ወያኔ የሚፈልጉትን እየሰጣቸው ስለሆነ፣ ነገሮች እንዲለወጡ የሚፈልጉበት ምክንያት የላቸውም፡፡ ለውጥ የሚፈልገው የተገፋው፣ የተጨቆነውና ተንቆ እንደ ከብት የሚነዳው፣ ሃብትና ንብረቱ የሚዘረፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው፡፡ ጥቅማቸው የተደላደለው የውስጥም ሆነ የውጭ ሃይሎች ግን ለውጥን አይፈልጉትም፡፡ ወያኔ/ኢሕአዴግ ምንም አይነት የኢትዮጵያዊነት ስሜት እንደሌለው፣ አገር አመራር ውስጥም የገባው አደናቅፎት ሳያስበው መሆኑን ከዚህ በፊት የሄደበትንና አሁንም የሚሄድበትን አቅጣጫ በማየት መገንዘብ

ይቻላል፡፡ ልብ ላለው! እብሪት፣ ዘረኝነትና ምቀኝነት ያልወጠረው ኢትዮጵያዊ ይህ ቡድን የሚያራምደውን ፖሊሲ በመመርመርና የሚሄድበትን አቅጣጫ በማየት በቅጡ ሊገነዘበው ይችላል፡፡በቂም በቀልና በምቀኝነት ተወጥሮ የሀገሪቱ ጥፋት ግድ ለማይሰጠው ‹‹እኔ ከሞተኩ ሰርዶ አይብቀል›› ባይ ግትር፣ ወደል፣ እውር አህያ ግን ይህን መገንዘብ ያሰቸግረዋል፡፡ ጥቅሙን የሳጣዋላ! በቅዠት ሰመመን የሚያልመውን የጎሳ ትርምስ እንዳይሳካ ያደርግበታላ! የቡድኑን የበላይነት የሚፈታተንበት ይመስለዋላ! እኛ ከሌሎች እንበልጣለን የሚለውን የአጋሰሶች ብሂል ይፈታተንበታላ!

*እኔ መሻሻል፤ የምላቸው ግን፤ ከነዚህ የተለዩ ለውጦች ናቸው፡፡ ሕዝብን ነጻ በሆነ ትምህርት ከድንቁርና ነጻ ማውጣት፤ በሕዝብ መካከል፤ ሰላምን፤ መግባባትንና አንድነትን መፍጠር፤ ሕዝብ ሠርቶ ኑሮውን የሚያሻሽልባቸውን ጤናውን የሚጠብቅባቸውን ድርጅቶች ማስፋፋት፤ የያንዳንዱን ሰው የግል እምነትና ነጻነት አለመድፈር፤ ለሕግና ለአስተዳደር ከፍተኛ ቦታ መስጠት፤ የያንዳንዱን ሰው አውቀትና የተፈጥሮ ስጦታ፤ ማክበርና በተገቢው ቦታ ማዋል፤ እነዚህንና የቀሩትን የሕዝብ ፍላጎት የሚመለከተቱ እርምጃዎች፤ በርግጥ ታላቅ ለውጦች እላቸዋለሁ፡፡*
*አቤ ጉበኛ - አልወለድም አራተኛ እትም ሚያዝያ 2006*

ወያኔ/ኢህአዴግ የተባለው ቡድን የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥቅም ከማስጠበቅ ይልቅ የባእዳንን ጥቅም እያስጠበቀ ቢቻል ሃገሪቱንና ሕዝቧን በትእቢት ረግጦ ለመመዝበር፣ ካልሆነለትም ሃገሪቱን አውድሞ ብሩን ወዳሸጋገረባቸው የምዕራቡ አለም ከተሞች ለመፈርጠጥ ቆርጦ የተነሳ የወንበዴዎች ጥርቅም ለመሆኑ ባለፉት ሃያ-አምስት አመታት ባገሪቱና በሕዝቧ ሕልውና ላይ የፈጸሙው የድፍረት፣የንቀት፣ የምቀኝነት፣ የአውዳሚነት ተግባሮች ግልፅ ማስረጃዎች ናቸው፡፡ ኢትዮጵያን ከጥቅማቸውና ከሰይጣናዊ ምቀኝነታቸው አንፃር የሚመለከቱ በርካታ ሆዳሞች ግን በከፍተኛ ደረጃ አገሪቱ ውስጥ እድገት እየታየ ነው በማለት ሀገሪቱን፣ ነፃነቷንና ክብሯን በመሸጥ ላይ የሚገኙትን ወንበዴዎች ሲያበረታቱና ሲተባበሩ እንሰማለን፡ ፡ በእርዳታና በብድር በገፍ ከሚላክላቸው ገንዘብ አብዛኛውን ውጭ አገር ወደሚገኙ የግል የባንክ ሂሳቦቻቸው አስገብተው በተረፈው የሙስና፣ የሌብነት፣ የወገንተኝነትና የማንአለብኝነት ዘላቂነት የሌለው የማስመሰል ኢኮኖሚ ስለገነቡ እድገት አመጡ እየተባለ ይለፈፋል፡፡ በእውነት ይህን አይነቱ አይን ያወጣ ብዙሀኑን የህብረተሰብ ክፍል ዘመናዊ ባሪያ ያደረገና ሕዝቡን የናቀ ተራ የሌብነት እድገት ይዘልቃል? ባገር ውሰጥም ሆነ በውጭ የሚገኙ አወቅን ባይ ማይሞች ናቸው እድገት አለ ሲሉ የሚደመጡት፡፡ ውጭ ያሉት በተዘረፈ ገንዘብ በካድሬነት ለሚያበረክቱት አገልግሎት የሚሰጣቸውን ጉርሻ እንዳይጎድልባቸው በሃሳብም ሙሉ በሙሉ ምዝበራውን ስለሚደግፉ ቁንጣን እንደያዘው አጋሰስ በየሚዲያውና በኢንተርኔቱ ሲያናፉ ይታያሉ/ይደመጣሉ፡፡ አገር ውስጥ ያሉትም በየመሸታ ቤቱ እየተርመጠመጡ ውስኪ እንደ ውሃ ሰለጨለጡና ጮማ ስለቆረጡ፤ ስጋዊ ፍላጎታቸውን በድህነት በሚማቅቅ ህዝብ መሃል ሰላረኩ የነሱ ያለገደብ ማለልና መንደላቀቅ መቻል እድገት የሚመስላቸው ናቸው፡፡ ነፃነት አጣን ብለው ጠመንጃ ያነሱ እኩዮች አሁን ነፃ ሆነው እንደፈለጉ መሸርሞጥ (ቃሉን በግብረስጋ ግንኙነት ብቻ አልወስነውም - የሕሊና ሸርሙጥናንም ያጠቃልላል) ስለቻሉ ሌሎችን ነፃነት ለመንፈግ አለመቦዘናቸው የቱን ያህል የእንስሳ --ከእንስሳም--የእባብና የእሪያ ባህሪ እንደተላበሱ ያመለክታል፡፡

እድገት የግብስብስ ቁሳቁስ መብዛት የሚመስላቸው፣ ላይ ላዩን እየጋለቡ ምእራባውያን ያደረጉትን ሁሉ እንደዝንጀሮ መቅዳት ሙያ ነው ብለው የሚያስቡ፣ ጥራቱን ያልጠበቀ፣ በእቅድና ጥናት ያልተመራ ሕንፃና መንገድ ስለተደረደረ የሕብረተሰቡ የሕይወት ደረጃ መሻሻል አሳይቷል ብለው ራሳቸውንም ሌሎችንም በእብሪት ለማሳመን የሚሞክሩ፣ አገር ውስጥ ማምረት የሚቻለውን ቁሳቁስ ከውጭ ስለተግበሰበሰና ሸቀጥ ሰለበዛ ለአገሪቱ የሚጠቅም የሚመስላቸው ማይሞች ጥቂት አይደሉም፡፡ በእርግጥም የነሱ ትምሕርት የጌቶቻቸውንና የሆዳቸውን ፍላጎት ለማሟላት እንጂ በአእምሯቸው በቅጡ እንዲያስቡበት እንዳልሆነ ተግባራቸው ይመሰክራል፡፡

በፍጥነት እያደገ የሚገኝ አኮኖሚም ይሉታል፡፡ በፍጥነት እያደገ የሚገኝ ምዝበራ መሆኑን ያልተረዳን ይመስል! የሀገር ቅርስ እየተሸጠ፣ በጨረታ እየተቸበቸበ መሆኑን የማናስተውል ይመስል! የዚህ አባባል አቀንቃኞች በውነት የሃገሪቱ የተፈጥሮ ሃብት ውድመት፣ የብዙሃኑ ኢትዮጵውያን እርዛት፣ ያብዛኛው ሕዝብ መቆርቆዝና የጥቂቶች አለቅጥ መንደላቀቅ፣ የዜጎቿ ወደ ድህነት መገፋት፣ የቅን አስተዳደር ጉድለት፣ የሙስና በከፍተኛ ደረጃ መስፋፋት፣ የሕዝብን በገፍ ስደትና ተስፋ መቁረጥ ማስተዋል የሚችሉ አይመስለኝም፡፡ ደነዞች ናቸውና! ‹‹የተመቸው ሁሉ ለሰው መች ይሳሳል›› ሆነና የሃገሪቱን ጥቅም ከራሳቸው መጠቀም፣ የህዝቧን ኑሮ ከራሳቸው የተንደላቀቀ የኑሮ ሁኔታ ጋር በማምታታት፣ ከውጭም ከውስጥም በሚደረግላቸው የጥቅም ማስጠበቅ ድጋፍ ራሳቸውን ሸጠው ሲዋሹ፣ ሲያታልሉ፣ በሃሰት ሲመሰክሩ፣ በሚያሳዝን ብልግናና ቅሌት ሲርመጠመጡ ይታያሉ፡፡ የሃገሪቱ ሃብት በፍጥነት ከተመዘበረ ኢኮኖሚዋም

በፍጥነት ማደጉ አይቀርም፡፡ ይህ ሲሆን ግን አገር ተሻሻለች፣ የብዙሀኑ ሕዝብ የኑሮ ደረጃ አደገ ማለት እንዳልሆነ ለመገንዘብ ከእኩይነትና ከእንከፍነት መንፈስ መላቀቅ ያስፈልጋል፡፡

በፍጥነት እያደገ የሚገኝ አኮኖሚ የሕዝብን የኑሮ ሁኔታ ከማባባስ ይልቅ ማስተካከል የለበትም ወይ? ብሎ ራሱን ላልጠየቀ የተባለው እድገት ለሃገር የሚጠቅም ሊመስል ይችላል፡፡ በእውነትም ኢትዮጵያ ውስጥ በተለይም ባለፉት 10 ዓመታት አኮኖሚው በፍጥነት ማደጉን የሚክድ ያለ አይመስለኝም፡፡ ችግሩ ይህ እድገት ዘላቂነት ከሌለው የተፋጥሮ ሃብት ምዝበራ፣ ሊሸጥ የሚቻለውን ሁሉ የሃገሪቱን አንጡራ ሃብት የህዝቡን እጅ ጠምዝዞ በግድ ከመሸጥ የመጣ ነው ወይስ ከእውነተኛና የተመጣጠነ የህዝብን ፍላጎት ያገናዘበ እድገት? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ያስፈልጋል፡፡

መርመጥመጥና መተራመስ ነው እድገት? ማታለል፣ መመዝበር፣ ማስመሰል ነው እድገት? የጥቂቶች ቅጥ ባጣ ሁኔታ መንደላቀቅ፣ የብዙሃኑ መግቢያ መውጫ ማጣት፣ ተስፋ መቁረጥና መሰደድ ነው እድገት? የተፈጥሮ ሃብትን እያወደሙ፣ ተፈጥሮን እየበከሉ ሕዝብን ለበሽታና ለስቃይ እየዳረጉና እያፈናቀሉ ነው እድገት? የአገርን ጥቅም ለሌሎች አሳልፎ መሸጥ ነው እድገት? ይህንንማ ቅኝ ተገዝተው ነፃ በወጡት የአፍሪካ አገሮች ያየነው ነው፡፡ ባገራችንም ጣሊያን ለአምስት አመታት በቆየበት ወቅት ሳገዛዝና የበላይነቱን ለማስከበር እንዲመቸው ባከናወናቸው እንቅስቃሴዎች የተነሳ የኢኮኖሚ እድገት ምልክቶች ታይተው እንደነበር አይዘነጋም፡፡ በዚህም አጋጣሚ ከፋሺስቶች ጋር ስለተባበሩ አልፎላቸው ፍርፋሪ የደረሳቸው ብዙዎች ነበሩ፡፡ እነሱም የራሳቸውን ድሎትና ሀብት በማየት አገሪቱ ውስጥ እድገት አለ ብለው መስክረው ነበር፡፡ ለብዙሃኑ ሕዝብ ግን ከተገዢነት ሌላ ምንም እንዳላሰገኘ ታሪክ ምስክር ነው፡፡

በተራ ሌብነት የረቀቀ ችሎታውን ያስመሰከረው የወያኔ/ኢህአዴግ ቡድን ላገዛዝ ይመቸኛል ያላቸውን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በሙሉ በቁጥጥሩ ስር አድርጎ በመምራት ከፍተኛ ገቢ ለአባሎቹና ለተባባሪዎቹ እያሰገኘ ነው፡፡ አገር ግን ተመዘበረች እንጂ አልተጠቀመችም፡፡ በብድር ጫና ጎብጣ ሕዝቧ ቆረቆዘ እንጂ ከድሕነት አልተላቀቀችም፡፡ ሳይሰሩ የከበሩ ቀፈታሞች በዙ እንጂ ለሀገሪቱ ዘለቄታዊ ጥቅምን የሚያረጋግጥ ስራ አልተሰራም፡፡ እንዴውም ለወደፊት ነቅርሳ ሊሆኑ የሚችሉ ችግሮች በሰፊው ተተክለው ለመፈንዳትና ሕብረተሰቡን ለማተራመስ ጊዜያቸውን እየጠበቁ ነው፡፡ በተባለው የማስመሰል የእድገት እንቅስቃሴ ውስጥ በሚፈጠረው የስራም ሆነ የድለላ እድል የሚያልፍላቸው እንደሚኖሩ አይጠረጠርም፡፡ እነሱ ስላለፈላቸው፣ ዘመዶቻቸው ስራ ስላገኙ ወይንም ፍርፋሪ ስለደረሳቸው ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ አልፎለታል በማለት የሰሚ ጆሮ ማደንቆር ከደነዝ እእምሮ የሚመነጭ አስተሳሰብ ነው፡፡ ባንፃሩ ግን የሚገፉ፣ የሚፈናቀሉ፣ የሚጉላሉና ለቋሚ ድህነት የሚጋለጡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ናቸው፡፡
እዚህ ላይ ብዙዎች የሚሳሳቱት ስህተት ስራ ስለተሰራ ለምን እንቃወማለን? በማለት የሚያሰሙት ጩኸት ነው፡፡ የኔም ሆነ የሌሎች ተቃዉሞ ስራ በመሰራቱ ወይም የውጭ ኢንቨስትመንት በመግባቱ ላይ አይደለም፡፡ በመጀመሪያ እንቅስቃሴው ለተወሰኑ ቡድኖች በቅድሚያ ተዘጋጅቶ ሕዝብ ሳያውቀውና ሳይስማማበት መተግበሩ፤ ቀጥሎም እንቅስቃሴዎቹ የኢትዮጵያን ሕዝብ ፍላጎት ሳያገናዝቡ፣ የተወሰኑ ሰዎች ለጥቅም (ፖለቲካዊም ሆነ የግል ጥቅም ሊሆን ይችላል) ስለፈለጓቸው ብቻ የሚፈፀሙ መሆናቸው ነው፡፡

አገሪቱ ውስጥ የሚፈሰው በእርዳታም ሆነ በብድር የሚመጣው ገንዘብ መጠን በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ ገንዘብ አብዛኛው በታቀደው ስራ ላይ አለመዋሉን ለመገንዘብ አዲስ አበባን መመልከት ይበቃል:: በከፍተኛ ወጪ ተሰሩ የሚባሉ መንገዶችና ሌሎችም የመሰረተ ልማት እንቅስቃሴዎች ባጭር ጊዜ ውስጥ ከጥቅም ውጭ ሆነው ማየት የተለመደ ነው፡፡ በከተማዋ ውስጥ ቅጥ ባጣ ስርአት በመደርደር ላይ የሚገኙት የሕዝብ ቤቶች (ኮንዶሚኒየም) የጥራት ደረጃ አሳሳቢና መመዘኛዎችን ያልጠበቀ ለመሆኑ ቀርቦ ያያቸው ያውቀዋል፡፡

በሌላ በኩል ባሁኑ ሰአት በየቦታው ተሰርተው ያለቁትን የግል ሕንፃዎች ብንመከት አብዛኞቹ የተሰሩት የዛሬ ሃያ አምስት አመት ኪሳቸው ቤሳ ብስቲን ባልነበራቸው ግለሰቦች ነው፡፡ እስኪ ራሳችንን እንጠይቅ፡፡ እንዴት ነው በእውቀት ቢሰተካከሉ እንኳን ከሌሎች ከስልጣናቸው ወይም ከጎሳና ከቡድን ግንኙነታቸው ሌላ በምንም መመዘኛ ሊበልጡ የማይችሉ ሰዎች በሚሊዮን የሚገመት ገንዘብና ንብረት በዚህ ጊዜ ውስጥ ሊያፈሩ የቻሉት? መጠቃቀምና ሙስና በህቡእ ባለበት ሁኔታ እንዲህ አይነቱ በሌብነት የመበልፀግ ክስተት ከብዙ በጥቂቱ ቢታይ ለመረዳት አያስቸግርም፡፡ የሚያሰደነግጠውና የሚያሳዝነው ሁኔታ ግን ይህ ተግባር በሰፊው ገሃድ የሆነ ድጋፍ ተሰጥቶት ከላይ እስከታች የገዢው ቡድን አባላት ዘመዶቻቸውና ደጋፊዎቻቸው የተዘፈቁበት መሆኑ ነው፡፡

ከተመደበለት በጀት አብዛኛውን ገንዘብ በልቶ ጥራቱን ያልጠበቀ መንገድ መስራት፣ አቅድ በሌለው አኳኋን ልፍስፍስ ሕንፃ መደርደር፣ ዘላቂነት በሌለው መንገድ የሃገርን የተፈጥሮ ሃብት መመዘበርም ለሚባለው የአኮኖሚ እድገት አስተዋፅኦ ያደርጋሉ፡፡ እውነተኛ እድገት ግን ቅድሚያ የሚሰጠው ለብዙሀኑ ኖሮ መሻሻል፣ ሕዝብን ነፃ ለማድረግና ከድንቁርና፣ ከበሽታ፣ ከማይምነትና ከተገዢነት ለማላቀቅ ለሚደረግ ጥረት መሆን ነበረበት፡፡ ነፃነቱን ያሰከበረ፣ በእውነተኛ የዲሞክራሲ መርሕ የሚመራ፣ ከድህነት፣ ከበሽታና ከማይምነት የተላቀቀ ሕዝብ ማሰብ ስለሚችል ማመዛዘን ይችላል፡፡ ማመዛዘን ስለሚችልም የሚጠቅመውን ያውቃል፣ የልማት እንቅስቃሴዎችንም ይዘትና አቅጣጫ በሚጠቅመው መንገድ በእርጋታ ይወስናል፡
፡ ዋናው ቁም ነገር፣ እድገት ያለነፃነት ዘላቂነት የሌለው መፍትሔ መሆኑን መገንዘብ ነው፡፡ እንኳን ተርቦና ኑሮ ጠምበት በበታችነት እየታየ ቀርቶ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉም ነገር በሚገባ ተሟልቶለት፣ ሳይራብ የሚኖርበት ሁኔታ ቢፈጠር እንኳን ባርነትን የሚቀበል ሕዝብ አልነበረም፡፡ ዛሬ ግን አምኖ ሰተት ብለው ስልጣን እንዲቆናጠጡ የፈቀደላቸውን ሕዝብ በንቀት እየረገጡ የሚንደላቀቁና እብሪት የወጠራቸው መዥገሮች አልለቅ ብለውት ይማቅቃል፡፡

ባለፉት ሃያ አምስት አመታት የታየው የሃገር ምዝበራና የሃብት ቅርምት በሌቦች ምስክርነት በከፍተኛ ደረጃ ድጋፍ ተሰጥቶት ውሸት በዝቶ እውነት አየጠፋች ሃገሪቱ የቅሌታሞች አገር እየሆነች ነው:: የሚታመኑ አሮጊቶችና ሽማግሌዎች እየጠፉ የሄዱባት፣ ሕዝብ ፊት አይን ያወጣ ውሸት ለመናገር የማያፍሩ ባለሥልጣናት የፈሉባት፣ ሀቅ አገር ለቆ የተሰደደባት፣ እውነተኛ ሰው ለማግኘት የማይቻልባት አገር ስትሆን እንዴት ነው እውነተኛ እድገት ሊመጣ የሚችለው? ፍትህና ርትእ የሌለባት የውሸት ምስክርነት የገነነባት ሃገር እንዴት ነው የሚጠቅማትን እድገት ማሳካት የምትችለው? ሌባ እንደቁም ነገረኛ እየታየ ሲበረታታ በሚታይባት አገር እውነትንና እድገትን ከየት ነው ማግኘት የሚቻለው? ዋሾነት፣ መልቲነት፣ ሌብነት፣ አታላይነት፣ አጭበርባሪነት እንደ ተሰጥኦ ተቆጥሮ ወሮ በላ አታላዮች እንደቁም ነገረኞች በሚወደሱበት ዘመን እድገት ከየት ሊመጣ ይችላል? ወጣቱ ትውልድም የዚህ አይነቱ ልክፍት ተጠናውቶት ለሃገር የሚያስብ ሳይሆን የግል ጥቅሙን ብቻ የሚያሳድድ፣ ይሉኝታን የማያውቅ፣ መልቲ፣ አታላይ፣ አስመሳይ፣ ለማኝ፣ ፈሪ፣ ሊያሸንፍ የሚችለው ላይ በእብሪተኛነት የሚደነፋ፣ ሊያሸንፈው ለሚችል የበላይ ደግሞ እንደ ተገራ እንስሳ የሚያጎበድድ፣ ወላዋይ፣ ግድ የለሽ፣ ራስ ወዳድ፣ ቅሌታም፣ ምቀኛ፣ ዋሾ፣ ሰነፍ፣ ክፉ ትውልድ እንዲሆን አየተገፋ ነው፡፡

አኩሪና ሊበረታታ የሚገባው ባሕላችን እየጠፋ፣ አገሪቱ ብታዳብረው ይጠቅማት የነበረው ጥሩ ጥሩው ሥነሥርዐት በጭራሽ እንዳይኖር እየተበረታታ ነው፡፡ አመጣጡን፣ ባሕሉን፣ ወጉን፣ እርሱነቱን ረስቶ የሌሎችን ማምለክ የተጠናወተው ሕዝብ ደግሞ ላገር ወስጥ የጭቆና አገዛዝም ሆነ ለአጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ የተመቸ ነው፡፡ ይህች ለቅኝ ገዢዎች አልያዝ አልጨበጥ ብላ ለሌሎችም ምሳሌ በመሆን ቅኝ አገዛዝን ለማክሰም የጎላ ሚና የተጫወተች አገር ዛሬ ለዘመናዊው እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ የገበሩ ሕዝቦች ምሳሌ እየሆነች ትገኛለች፡፡

ባለፉት ሃያ አምስት አመታት ኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በርካታ ያፍሪካ አገሮች ውስጥ የታየው ክስተት ዓለም የቱን ያህል ፊቱን ጥሬ ምርት ፍለጋ ወደ አፍሪካ እንዳዞረ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ የበለፀጉ ሀገሮች ቻይናና ሌሎችም አገሮች ኢትዮጵያ ውስጥ ለጥቅማቸው ሲሉ የሚገፋፉት፣ ለነሱ ጥቅም ሲባል የተቀየሰ ኢንቨስትሜንት አየተፋጠነ ነው፡፡ ሆኖም ይህ ኢንቨስትሜንት ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሚጠቅም መልኩ ስላልተቀናበረ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከሚሰጠው ጥቅም ይልቅ ለበእዳኑ የሚሰጠው ጥቅም እየበረታ አገሪቱን ግን ለከፋ አደጋ እያጋለጠ የሄደበት ሁኔታ ይታያል፡፡

ይህ አፍሪካ ላይ ያነጣጠረ ጥሬ ምርት ፍለጋ ላይ ያተኮረ የምዝበራ አኮኖሚ ለባእዳኑ ከፍተኛ ጥቅም እንዳለውና ለኢትዮጵያ ግን አስከፊ ሁኔታን ሊፈጥር እንደሚችል መዘንጋት እንከፍነት ነው፡፡ ሃገሪቱ ላይ እየተስፋፉ የሚገኙትን ‹‹የእድገት›› እንቅስቃሴዎች ስንመለከት፣ ማየት ከቻልን፣ ግልጽ የሚሆንልን ነገር እየተስፋፋ የሚገኘው በሀገሪቱና በሕዝቧ ጥቅም ላይ የተመረኮዘ የእድገት እንቅስቀሴ ሳይሆን ሌሎች ከራሳቸው ጥቅም አንፃር ለሃገሪቱ ያስፈልጋታል ብለው የሚግቱን እንቅስቃሴ ነው፡፡ መልካም አመራር ቢኖር ይህን ድርጊት መቋቋም ይቻል ነበር፣ ለሃገሪቱ በሚጠቅም ሁኔታ ማደላደል ይቻል ነበር፡፡ ራሱን የሸጠ አመራር ግን ይህን መብቱን የማስከበር ችሎታ ሊኖረው አይችልም፣ በባሕሪው ባንዳ አገር ሻጭ ወንበዴ ነውና!

እዚህ ላይ ናይጀሪያን እንደምሳሌ መውሰድ ይቻላል::

በነዳጅ ሃብቷ የታወቀቸው ናይጀሪያ ለብዙ አመታት ከዚህ ቅርሷ ተጠቃሚው ሕዝቧ ሳይሆን የውጭ ኩባንያ ዎችና ስግብግብ መሪዎቿ መሆናቸው ግልፅ ታሪክ ነው::
ነገር ግን በፍጥነት እያደገ የሚሄድ አኮኖሚ ነበራት፡
፡ ዛሬ የናይጀሪያ ሕዝብ የተሻለ ሁኔታ ላይ ነውማለት ግን አይቻልም::
ከውጭ ኩባንያዎችና መንግስታት ጋር በሚደረግ የጥቅም ግንኙነት ለዘመናት ሃብቷ እየተመዘበረ ስለኖረችና የሕዝቧ መሰረታዊ የኑሮ ጥያቄዎች
ስላልተመለሱ የተወሳሰቡ አኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ የአካባቢ ብክለት ችግሮች ውስጥ ትገኛለች፡፡

ያሁኗ ኢትዮጵያም ሁኔታ ተመሳሳይ ነው፡፡ አገሪቱ በሯን በሰፊው ከፍታ በተገኘው ሁሉ በባእዳንና በአገር ውስጥ ደም መጣጮች ለመመዝበር ራሷን አዘጋጅታለች፡፡ የተፈጥሮ ሃብቷ፣ ቅርሶቿ፣ ማእድኖቿና ሕዝቧ ሳይቀር በከፍተኛ ፍጥነት በመዘረፍ ላይ ናቸው፡፡ ያለ ጥናትና እቅድ የውጭ ምንዛሪ ስለሚያስገኙ ብቻ ላገር የሚጠቅሙም የማይጠቅሙም እንቅስቃሴዎች ተፈቅደው በፍጥነት አያደገ ነው ለሚባለው
ኢኮኖሚ አስተዋፅኦ እያደረጉ ነው፡፡ የሚያስከትሉት የረዥም ጊዜ ጉዳት ግን በቅጡ አልተመዘነም፡
፡ ምእራባውያንና ቻይና እንዲሁም ሌሎች አገሮች ለጥቅማቸው ሲሉ የሚያበረታቱት እንቅስቃሴ ለነሱ በሚመች ሁኔታ ስለሚቀየስ ለሕዝቡ ዘላቂ ጥቅም ከማምጣት ይልቅ ጊዜ እየጠበቀ የሚያመረቅዝ ቁስልን መፍጠሩ የማያጠራጥር ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ የበይ ተመልካች ተደርጎ በጉልበት
የሚገፋው ህዝቧ እየተበደለ ምርቷ ማደጉ አይቀርም፡፡ ተያይዞም ኢኮኖሚዋ አደገ መባሉ አይቀርም፡
፡ ተጠቃሚዎቹ ግን ሕዝቦቿ ሳይሆኑ የውጭ ኩባንያዎች
መንግስታትና ተባባሪዎቻቸው እንዲሁም ባለስልጣናትና አጋሮቻቸው ናቸው፡፡

እዚህ ላይ ብዙዎች የሚከራከሩበት ነጥብ መንገድ ተሰርቷል፣ ፋብሪካዎች ተገንብተዋል፣ ከተሞች ሰፍተዋል፣ የግብርና ኢንቨስትሜንት ሰፋፊ መሬቶችን ምርት ሥራ ላይ ለማዋል አስችሏል፣ ቁሳቁስ እንደልብ ይገኛል ወዘተ... የሚሉ ናቸው፡፡ ሁሉም ነጥቦች ትክክል ናቸው፣ ተደርገዋል፣ መንግስቱም እነዚህን ብቻ ሳይሆን በሃያ አምስት አመታት ጊዜ ውስጥ ከዚህም በላይ ማድረግ ይጠበቅበት ነበር፡
፡ የሚታዩት እንቅስቃሴዎችን ባንክሮ ላያቸው ለተወሰኑ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች በፍጥነት ሃብት የሚያጋብሱበትን መንገድ የመፍጥር የተሰላ አቅድ እንደሆነ መረዳት አይከብድም፡፡ ዋናው ቁም ነገር በመጀመሪያ ደረጃ እነዚህ ሁሉ የልማት እንቅስቃሴዎች የሃገሪቱን ተጨባጭ ችግሮች በተለይም ድህነትንና፣ ረሃብን ለማጥፋት የረዱ ሳይሆን እንዴውም በብዙሀኑ ድሃ ሕብረተሰብና በጥቂቱ ሃብታም ሕብረተሰብ መሃከል ያለውን ቅጥ ያጣ ልዩነት የሚያሰፉ እንጂ የሚያጠቡ አለመሆናቸው ነው፡፡ የተዘረጉትን የልማት እንቅስቃሴዎች ስንመለከት የህዝብን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል፣ ረኃብን ለማጥፋት፣ ድንቁርናን ለመከላከል ሳይሆን ስልጣንን ለማራዘምና ይህን ስልጣን ለማራዘም የሚረዱትን የውጭ ኃይሎች የሚፈልጉትን በመስጠት ተባብሮ አገር መመዝበር ነው፡፡

ኢትዮሚድያ - Ethiomedia.com
November 29, 2016